ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፤
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዝእተብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

**ቍጥር ፲፱/፳፻፱ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**

**በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥ ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡**

**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**

**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።**

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤
እግዝእተብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤
በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥
እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ካህናችን፥
ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡
በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

**+ + +**

## ይድረስ፡-

**በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥**
**በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥**
**በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡**
**የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥**

**ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና**
**በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥**
**በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥**
**በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥**

**ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡**
**የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡**
**"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡**
**በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥**

**በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡**
**የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡**
**ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!**
**እንዲሁም፡**
**የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡**
**በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥**
**ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥**
**በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!**

**በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!**

# መቅድም

በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ቃል ከተነገረው፣ ካለፈው፡ ከ፲፯ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ በፊት፡ ይፋ እንደወጣው፡ እንደ፲፮ኛውና ከእርሱ እንደቀደሙት ተከታታይ መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎቼ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዝእተብሔራችሁና ሃይማኖታችሁ፥ መድኃኒታችሁና ክህነታችሁ፥ እናታችሁና ንግሥታችሁ፥ አገራችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ።**

## የዚህ ዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ ምክንያት።

በአኹኑ ጊዜ፡ "መጽሓፍ ቅዱስ" የሚባለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ስብስብ፣ በተለይ፡ ብሉያቱ፡ እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች ሳይኾኑ፡ ራሳቸውን፡ "የእስራኤል ልጆች" የሚሉት፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ የጻፉት ስለኾነ፡ የኢትዮጵያ ልጆች መጽሓፍ አይደለም። ይህም እውነታ፡ የገናናዎቹ እና የስመ-ጥሩዎቹ፡ የእነመልከ-ጼዴቅ እና የእነንግሥት ማክዳ፣ እነርሱን የመሰሉትም ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ዜና-መዋዕል እና ዝክረ-ነገር፡ ተሟልቶ እና ተስተካክሎ የተመዘገበበት ባለመኾኑ ጭምር፡ ተረጋግጦ ይታወቃል።

ባለፈው [በ፲፰ኛው] የዐዋጅ ቃሌ የገለጽሁላችሁን ኹሉ፣ ይህንኑ የዐዋጅ ቃሌን፡ በእኛ በእግዚአብሔር እውነት እና በመንፈስ-ቅዱስ አምልኳችሁ የሰማችሁ ኹሉ፡ በማስተዋል ተረድታችሁታል፤ አምናችሁም ተቀብላችሁታል። ይኸውም፡ ከመጀመሪያው፡ "የሰው ልጆች" ከተባሉት ፍጡሮቻችን መካከል፡ "ቅዱሳት መጻሕፍት"፥ "መጽሓፍ ቅዱስ"፥ "ድርሳናት"፣ "ተአምራት"፣ "ገድላት" በሚሏቸው የጽሕፈት መዝገቦቻቸው ውስጥ፡ የእኛ የእግዚአብሔር እንደኾኑ፣ በማስመሰል፣ ያም ብቻ ሳይኾን፡ እንደኾኑም አድርገው፡ የጻፏቸው፡ ብዙ የሓሰት ነገሮች መኖራቸውን ነው።

በዚህ ረገድ ያሰማኋችሁን የዐዋጅ ቃሌን፡ በማስተዋል ተረድታችሁ እና አምናችሁ ልትቀበሉት የቻላችሁት፡ ያለምክንያት አይደለም። ምክንያቱ፡ ግልጽ ነው፡- ከእነዚያ የሰው ወገኖች ተለይታችሁ፡ በቅድሚያ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፣ ቀጥሎም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት፣ እናንተ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡ የእኛ የእግዚአብሔር፡ ሕያዋን መጻሕፍት በመኾናችሁ ነው።

አዎን! እውነት እውነት እላችኋለሁ! የእኛ የእግዚአብሔር እውነት እና የመንፈስ ቅዱስ ቃሎች የሚጻፉት፡ እየራሳቸውን፡ ሙታን ባደረጉት፡ በሰው ልጆች እጅ እና በድን በኾነው ብራና ላይ ሳይኾን፤ እኛ እግዚአብሔር ራሳችን፡ በመንፈስ ቅዱስ እጃችን፡ በሥነ-ተፈጥሮ ሥርዓታችን በምንከትብባችሁ፤ በእኛ፡ ሕያዋን በኾናችሁት፤ በእናንተ፡ በእያንዳንዳችሁ ውሳጣዊ የሰውነት ሰሌዳ ላይ ብቻ ነው።

ይህንም እውነታ፡ ገና ጥንት፡ በነቢያችን ባስነገርነው፡ "ይቤ እግዚአብሔር፦...'እወዲ ሕግየ፡ ውስተ ኅሊናሆሙ፤ ወእጽሕፎ፡ ውስተ ልቦሙ። ...ወኢይምህር እንከ፡ እኁ፡ እኅዋሁ፡ እንዘ ይብል፦ «አእምርዎ ለእግዚአብሔር!» እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፤ ንኡሶሙ፥ ወዐቢዮሙ።' እግዚአብሔር አለ፦ '<u>ሕጌን፡ በልቡናቸው አሳድራለሁ፤ በኅሊናቸውም እጽፈዋለሁ። ...ከዚህ በኋላ፡ «እግዚአብሔርን ዕወቀው!» ብሎ፡ አንዱ፡ ለአንዱ፡ ወንድሙን የሚያስተምር የለም፤ ታናሹም፥ታላቁም፥ ኹሉም፡ እኔን ያውቁኛል</u>።'" በሚለው ቃላችን፡ እናንተ፡ ታማኞቼ፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን ኢትዮጵያውያት እና ኢትዮጵያውያን አውቃችሁታል። (ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬። ዮሐ. ፮፤ ፵፭።)

ይህ ከመኾኑ የተነሣ፡ የእኛ የእግዚአብሔር የኾነውን ቃል፤ ከእኛ ያገኛችሁትንም ዕውቀት እና ሥርዓት፥ ሃይማኖት እና ምግባር ጭምር፡ ቀድሞም፡ ጠብቃችሁ እና ተከትላችሁ፤ አጽንታችሁ እና ሕይወት አድርጋችሁ የኖራችሁት፤ አኹንም እየኖራችሁ ያላችሁት፤ ወደፊትም የምትኖሩት፡ እናንተው፤ ከእነዚያ የሰው ወገኖች ተለይታችሁ፡ በቅድሚያ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፤ ቀጥሎም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት፤ እናንተ፡ የእኛ የእግዚአብሔር፡ ሕያዋን መጻሕፍት የኾናችሁት፤ አዎን! የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ብቻ ናችሁና፡ ከዚህ ማንነታችሁ እና ምንነታችሁ ሳትነዋወጹ ልትቀጥሉበት ያስፈልጋችኋል።

አኹን፡ ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ መነሻ የኾነኝን ምክንያት ልግለጥላችሁ፦ እሱም፡ ባለፉት ዐዋጆቻችን እንዳደረግሁት፤ አኹንም፡ በዚህ ረገድ፡ ስላለው፤ የሰው ወገኖች ስላማሰኗት፡ ስለእኛ የእግዚአብሔር እውነት፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ባግባቡ እየከሡትሁ እና እያብራራሁ ማሳወቄን የቀጠልሁ መኾኔን እንድትገነዘቡት የማድረጉ አስፈላጊነት ነው።ከዚህ በታች ቀጥዬ የማሰማችሁ፡ ከዚሁ ርእሰ-ጉዳይ ጋር የተያያዘው፡ አንድ ቍም-ነገር፡ ይህን እውነታ፡ አጕልቶ እና አረጋግጦ ያስረዳችኋል።

አረጋግጦ የሚያስረዳችሁም፡ እኔ፡ እግዝእተብሔር እም እናታችሁ፤ በተዋሓድኋት እኅታችሁ፡ ድንግል ማርያም ሰውነት፡ መድኃኒታችሁ እና አገራችሁ ኢትዮጵያን ኾኜ፡ በንግሥትነት፤ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድም፡ በፈጣሪነት አባትነቱ እና በኢየሱስ መሲሕ ወንድምነቱ፡ ሰላማችሁና ካህናችሁ ኾኖ፡ በንጉሥነት፡ እነሆ፡ ኹለታችንም፡ በእኛ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ በገሃድ በተገለጥንባት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አማካይነት እየተናገርናችሁ፤ እናንተም፤ በእውነትና በመንፈስ አምልኳችሁ፡ በነፍስ፤ በሥጋ እና በመንፈስ ጆሮዎቻችሁ የምትሰሙት ቃላችን ነው። አዎን! ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ መነሻ የኾነኝ ምክንያት፡ ይህ ነው።

# ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ-አምልኮ፡-
# የኢትዮጵያው መልከ-ጼዴቅ፡
# ኅብስተ-አኰቴት እና ጽዋዓ-በረከት ሥርዓት።

እነዚያ የሰው ወገኖች፡ "ቅዱሳት" ብለው በሰየሟቸው መጽሓፎቻቸው ውስጥ፡ ያማሰኗትን፡ የእኛን የእግዚአብሔርን እውነት፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ባግባቡ እየከሠትሁና እያብራራሁ፡ ልነግራችሁ የተገለጥሁባቸውን፤ ይህንኑም፡ ለእናንተ እና ለፍጥረታተ-ዓለማቱ ማሳወቄን የቀጠልሁ መኾኔን የምትገነዘቡባቸው፤ ከዚሁ ርእሰ-ጉዳይ ጋር የተያያዙት እና በሰዎች ዘንድ፡ ጥቃቅን የሚመስሉት፡ አንዳንዶቹ ቍም-ነገሮች፡ እኚኸውላችሁ! ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. የአዳም እና የሔዋን የመጀመሪያ እና ተከታይ ወንዶች ልጆች ኾነው፡ ከመንትዮቻቸው ሴቶች ልጆች ጋር ስለተወለዱት፡ ስለቃየል [ቃይ-ኤል] እና ስለአቤል [አብ-ኤል] ማንነት እና ስለሙያቸው፥ ለእኛ ለእግዚአብሔር፡ ስላቀረቡት መሥዋዕትም የሚተርከው ርእስ፡ በመጽሓፍ ቅዱሳችሁ፡ ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] በ፬ኛው ምዕራፍ፥ ከቍጥር ፩ እስከ፰ ባለው አንቀጽ ላይ ይገኛል። እሱም፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

**"ወአእመራ አዳም ለሔዋን ብእሲቱ፤ ወፀንሰት። ወወለደቶ ለቃየል። ወትቤ፡- 'አጥረይነ ብእሴ፡ ዘእግዚአብሔር!'**

**"ወደገመት፤ ወወለደቶ፡ ለአቤል እኁሁ።**

**"ወኮነ አቤል፡ ኖላዌ-አባግዕ። ወቃየልሰ፡ ኮነ መስተገብረ-ምድር።**

**"ወኮነ እምድኅረ ብዙኅ መዋዕል፡ አምጽአ ቃየል፡ እምነ ፍሬ-ምድር፡ መሥዋዕተ፡ ለእግዚአብሔር።**

**"ወአቤልሂ አምጽአ መሥዋዕተ፡ እምበኵረ አባግዒሁ፤ ወእምስቡሓኒሆሙ። ወነጸረ እግዚአብሔር፡ ላዕለ አቤል፤ ወላዕለ መሥዋዕቱ።**

**"ላዕለ ቃየልሰ፥ ወላዕለ መሥዋዕቱ፡ ኢነጸረ። ወአኅዘኖ ለቃየል ጥቀ፤ ወወድቀ ገጹ።**

**"ወይቤሎ እግዚአብሔር ለቃየል፡- 'ለምንት ተኀዘን? ወለምንት ወድቀ ገጽከ? አኮ በጽድቅ፡ ዘአምጻእከ ሊተ፤ ወርቱዕ፡ በጽድቅ ታምጽእ ሊተ። አበስከ።'**

"አዳምም፡ ሚስቱን ሔዋንን፡ በሩካቤ ሥጋ ተገናኛት፤ ፀነሰችም። 'የእግዚአብሔር የኾነ ሰው አገኘን!' የሚል ትርጉም ያለውን ስም የሰጠችውን፡ ቃየልንም ወለደች።

"ዳግመኛም፡ ወንድሙን አቤልን ወለደችው።

"አቤልም፡ የበጎች እረኛ ኾነ። ቃየል ግን፡ ገበሬ ኾነ።

"ከብዙ ዘመን በኋላ፡ እንዲህ ኾነ፦ ቃየል፡ ካመረተው የምድር ፍሬ፡ ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕት አቀረበ።

"አቤልም ደግሞ እንዲሁ፡ ከበጎቹ፡ በመጀመሪያ ከተወለዱት፣ ከሰቡትም መካከል መርጦ፡ መሥዋዕት አቀረበ። እግዚአብሔርም፡ ወደአቤል፣ ወደመሥዋቱም ተመለከተ፤ ተቀበለውም።

"ወደቃየል እና ወደመሥዋዕቱ ግን፡ አልተመለከተም፣ አልተቀበለውም። ይህም፡ ቃየልን፡ እጅግ አሳዘነው፤ ፊቱም ጠቈረ።

"እግዚአብሔርም፡ ቃየልን አለው፦ "ለምን አዘንህ? ለምንስ፡ ፊትህ ጠቈረ? መሥዋዕትህን ያቀረብህልኝ፡ በእውነት አይደለም፤ በእውነት ልታቀርብልኝ፡ በተገባህ ነበር። ስለዚህ በድለሃል።"

በዚያን ጊዜ፣ ከዚያም በኋላ፣ ምንጊዜም፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ሊቀርብልን የምንወድደው እና የምንሻው፣ የምንቀበለውም <u>መሥዋዕት</u>፡ በምንነቱ ዓይነት ላይ የተመሠረተ እና ያተኰረ ሳይኾን፣ ነገር ግን፡ ምንም ምን ይኹን፡ ያን መሥዋዕት የምንቀበለው፡ ራሱ፡ የመሥዋዕቱ አቅራቢ፡ የሚያቀርብበት፡ የነፍሱ ሃይማኖታዊ እውነተኝነት እና የሥጋው ምግባራዊ ቅንነት፣ የመንፈሱም ባሕርያዊ ንጽሕና፡ ፍጹም ኾኖ ስናገኘው ብቻ ነው።

ቀደም አድርገን፡ በአንዱ ኢትዮጵያዊ ነቢያችን አንደበት፡ "**ምጽዋተ አበድር፤ እመሥዋዕት፤ ወአእምሮ እግዚአብሔር፡ እምቍርባን።** እኔ፡ ላልበላው እና ላልጠጣው፣ ላልከብርበትም፡ ለእኔ ከምታቀርቡልኝ መሥዋዕታችሁ፥ ቍርባናችሁም ይልቅ፣ የእኛን የእግዚአብሔርን ማንነት በእርግጥ ዐውቃችሁ፡ ለሌላው የተፈጥሮ ወገናችሁ የምታደርጉለትን፡ በጎ ምግባራችሁን እወድደዋለሁ፤ እመርጠዋለሁም፤ ይኼ የበለጠ ያስደስተኛልና።" የሚለውን መመሪያ ቃላችንን ያስተላለፍንላችሁ፣ አዎን! ለዚህ ነው። (ሆሴ. ፮፥ ፮። ማቴ. ፱፥ ፲፫፤ ፲፪፥ ፯።)

የመሥዋዕቱ እና የቍርባኑ አቀራረብ፡ እንዴት ሊኾን እንደሚገባም፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ቀደም አድርገን ያናገርነውን፡ የሌላውን ኢትዮጵያዊ ነቢያችንን ቃል በማዘከር፡ ከዚያች፡ ውኃ ልትቀዳ፡ ወደገጠሩ የምንጭ ጕድጓድ ለመጣችው ሳምራዊት ሴት ያሳወቃት የአምልኮ መመሪያችን ያስረዳል።

ይኸውም፦ "**እመ እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን፡ ይሰግዱ ለአብ፡ በመንፈስ፥ ወበጽድቅ፤ እስመ አብኒ፡ ዘከመዝ የኅሥሥ፡ እለ ይሰግዱ ሎቱ። እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።**'

"በእምነትና በትክክል የሚያመልኩ ሰዎች፡ እግዚአብሔር አብን የሚያመልኩት፡ በመንፈስና በእውነት ነው፤ እርሱን፡ በእግዚአብሔርነቱ የሚያመልኩት ኹሉ፡ እንደዚህ፡ በመንፈስና በእውነት እንዲያመልኩት ይሻል። እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነውና፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ይገባቸዋል።'" የሚለው ነው። (ዮሐ. ፬፥ ፳-፳፮።)

በእነዚህ የነቢያቶቻችን ቃላት መሠረት፡ የመጀመሪያዎቹ ፍጡራን ሰዎቻችን የኾኑት፣ የቃየል እና የአቤል ወላጆችም ለመኾን የበቁት፡ አዳም እና ሔዋን፡ በእኛ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠሩበት መልካቸው እና "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኹኑ!" በተባሉበት ባሕርያቸው ያመነጩት፡ ለእኛ የሚያደርጉት፡ የመሥዋዕት እና የቍርባን አቀራረብን ያካተተ፡ የአምልኮ ሥርዓት ነበራቸው።

ይኸውም፡ ሕያዋን ለኾኑት ፍጡሮቻችን፡ መብል እና መጠጥ ኾነው፡ እነዚሁ ፍጡሮቻችን፡ ህልውናቸውን፡ በሕይወት እንዲቀጥሉ ይቻላቸው ዘንድ፡ ምድር፡ በሥነ-ፍጥረት ሥርዓት፡ በዝናብ አብቅላ፣ በነፋስ አሕይዋ እና በፀሓይ አብስላ፡ እንድትመግባቸው ካደረግነው የአዝርዕት እና የአትክልት፣ የፍሬያትም ምርት መካከል፡ በቀላሉ እና በብዛት ሊገኙ የሚችሉትን፡ የስንዴንና የወይንን የአዝመራ በረከት በመምረጥ፡ ከእነዚህ የእህል ነዶ ተጋግሮ የሚቀርበው ኅብስት፣ ከፍሬ ዘለላውም ተጨፍልቆ የሚወጣው ጭማቂ፡ ኅብስተ-አኰቴት እና ጽዋዓ-በረከት ኾኖ፡ በአዳም እና በሔዋን፡ ለእኛ ለእግዚአብሔር፡ በመሥዋዕትነት፣ በቍርባንነትም የቀረበበት፣ እኛም የተቀበልነው፡ ቀዳማዊው እና ደኃራዊው፥ አማናዊው እና ዘለዓለማዊው ሥርዓተ-አምልኮ ነው።

ቀደም ብዬ፡ "በዚያን ጊዜ፣ ከዚያም በኋላ፣ ምንጊዜም፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ሊቀርብልን የወደድነው፣ የምንወድደውም፣ የተቀበልነው፣ የምንቀበለውም መሥዋዕት፣ ቍርባንም፡ ይኼ ነው!" ያልኋችሁ፡ አዎን! በእውነት፡ ይኼ ብቻ መኾኑን፡ አኹንም፡ እንደገና በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ይኸው፡ አበክሬ ነገርኋችሁ።

በአዳም እና በሔዋን የተጀመረውንና የተመሠረተውን፣ እኛም እግዚአብሔር የተቀበልነውን፣ የቀደሙትን ምዝላቶቻችሁን ፈለግ ተከትላችሁ፡ ይህን፡ ቀዳማዊ እና ደኃራዊ፥ አማናዊ እና ዘለዓለማዊ የኾነ የኅብስተ-አኰቴት እና የጽዋዓ-በረከት ሥርዓተ-አምልኮ፡ ከሌሎቹ የሰው እና የመናፍስት ወገኖች ከኾኑት ፍጡሮቻችን ኹሉ ተለይታችሁ፡ እስከዛሬ አጽንታችሁ የጠበቃችሁ፥ አኹንም ሕያው አድርጋችሁ የቀጠላችሁት፡ እናንተ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን ብቻ ስለኾናችሁ፡ በዚህ ሃይማኖታዊ እና ምግባራዊ ጽናታችሁ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ አባታችሁ እና እናታችሁ፣ እኅታችሁ እና ወንድማችሁ፣ ቅዱሱ ጓደኛ መንፈሳችሁም፡ ምን ያህል ደስ እንዳለን፣ የዚሁ ደስታችን ተካፋዮች እንድትኾኑ በመፍቀድ፡ ይህን ብሥራታዊ [የምሥራች] ዜና፡ እኔው ራሴ፡ ይኸው፡ በዚህ የአዋጅ ቃሌ ላስሰማችሁ ወደድሁ።

የእኔ የኢትዮጵያዋ እግዝተብሔር እም ድንግል ማርያም ልጅ በመኾን፡ በዚህ ኢትዮጵያዊ ሰውነቱ የተገለጠው እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንት፡ የአዳም እና የሔዋን፥ ኋላም፡ የኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ እና የሳሌም የኾነውን፡ የኀብስተ-አኰቴት እና የጽዋዓ-በረከት ሥርዓተ-አምልኮ መከተልን ትተው፣ ደም በማፍሰስ የተጀመረውን፡ የአቤልን፡ መሥዋዕት እና ቍርባን አቀራረብን ወግ ተቀብለው፣ አጽንተውም በኖሩት፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ መካከል በነበረበት ጊዜ፡ በዚህ ረገድ፡ በመጨረሻው እና በዘለዓለማዊው፣ በአማናዊዉም መልከ-ጼዴቅነቱ፡ ያደረገውን እና የፈጸመውን፡ መለኮታዊ እና ትስብእታዊ ተልእኮ ታውቁታላችሁ።

ይኸውም፡ ደም በማፍሰስ የተጀመረውን፡ የአቤልን፡ የመሥዋዕት እና የቍርባን አቀራረብን ወግ ተቀብለው፣ አጽንተውም ለኖሩት፡ ለኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ራሱን፡ የመጨረሻው፡ የፋሲካቸው በግ እና ቍርባን አድርጎ፡ በመስቀል ላይ፡ በቤዛነት የሠዋላቸው መኾኑ ነው፤ እርሱም፡ "**ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፡ ዘየዐትት ኃጢአተ-ዓለም! የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሔር በግ ይኸውላችሁ!**" ተብሎ፡ በመጥምቁ መልእክተኛችን፡ በዮሓንስ ዘካርያስ ኤልሣቤጥ የተነገረለት፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ነው። (ዮሓ. ፩፥ ፳፱ እና ፴፮።)

እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ራሱን፡ እንዲህ፡ የመጨረሻው፡ የፋሲካቸው በግ እና ቍርባን አድርጎ፡ በመስቀል ላይ፡ በቤዛነት ከሠዋላቸው በኋላ፣ ይኸው፡ የአይሁድ፡ ደም የማፍሰስ ኦሪታዊ ሥርዓተ-አምልኳቸው፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ለአንዴ እና ለዘለዓለም ያበቃ፣ የተወገደም መኾኑን፡ በዐዋጅ አስታወቃቸው። ያስታወቃቸውም፡ በዚያ ቦታ፡ ያ ጥንታዊው እና አዳማዊው፣ ኢትዮጵያዊዉም፡ የኀብስተ-አኰቴት እና የጽዋዓ-በረከት ሥርዓተ-አምልኮ፡ እንደገና ተመልሶ የተተካ መኾኑን፡ በይፋ ባረጋገጠበት፡ ማኅተማዊ የኪዳነ-ምሕረት ሥራው ነው። (ዕብ. ምዕ. ፱ እና ፲።)

ይህንም፡ ዕፁብ ድንቅ ሥራውን ገልጦ ያሳየውና የፈጸመው፡ እንደኢትዮጵያ ልጆቹ ጥንታዊ ባህል፡ ቤተ-መቅደሳችን በኾነው፡ በአንዱ ኢትዮጵያዊ አማኙ መኖሪያ ቤት በተዘጋጀለት፡ በምሴተ-ሓሙስ የፋሲካ ገበታቸው ላይ እንጂ፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ የገበያ አዳራሽ፣ የወንበዴዎች እና የሌቦችም ዋሻ ባደረጉት፡ በሰሎሞንና በዘሩባቤል፣ በሄሮድስም ቤተ-መቅደሳቸው አይደለም። (ማቴ. ፳፮፥ ፲፯-፳፰። ማር. ፲፬፥ ፲፪-፳፭። ሉቃ. ፳፪፥ ፯-፳።)

ይኼ ቤተ-መቅደሳቸውማ፡ ከምን ዓይነቱ የርኵሰት እና የውርደት ዝቅጠት እንደደረሰ፣ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የተናገራቸው እንዲህ የሚሉት ቃሎቹ ያስረዳሉ፡-

**"ቤትየሰ፡ ቤተ-ጸሎት ትሰመይ! ወአንትሙሰ፡ ረሰይክምዎ፡ በዓተ-ፈያት፣ ወሰረቅት። ወኢትረስዩ ቤተ-አቡየ፡ ቤተ-ምሥያጥ!** ቤቴማ፡ 'የጸሎት ቤት' ተብላ ተሰይማ ነበር፤ እናንተ ግን፡ የወንበዴዎችና የሌቦች ዋሻ አደረጋችኋት።"

ይህን ካላቸው በኋላ፣ አከታትለው ላቀረቡለት የተንኰል ጥያቄ፣ እውነተኛው ቤተ-መቅደስ፡ ሰዎች የሠሩት ሳይኾን፣ እኛ እግዚአብሔር፡ በመልካችን እና "ከእኛ እንደአንዳችን ኾነ!" ብለን የፈጠርነው መኾኑን በማረጋገጥ፡ **"ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ-መቅደስ! ወበሠሉስ ዕለት፡ አነ አነሥኦ።** ይህንኑ ቤተ-መቅደስ አፍርሱት! በሦስተኛው ቀን፡ እኔ አነሣዋለሁ።" በሚል ቃል፡ ስለራሱ የሰውነት ሕንጻ ለተናገራቸው፡ ለተቃዋሚዎቹ እና ለገዳዮቹ አሪታውያኑ አይሁድ፡ በሚበቃ ዐሳውቋቸዋል።

ይኼንኑ፡ የቤተ-መቅደስ ሕንጻ፡**"ወወፂአ እግዚእ ኢየሱስ፡ እምቤተ-መቅደስ፣ ሖረ። ወቀርቡ አርዳኢሁ፤ ወአርአይዎ ንድቀ-ሕንጻሁ፡ ለቤተ-መቅደስ።** እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ፡ ከቤተ-መቅደስ ወጥቶ፣ እየኼደ ሳለ፣ ደቀ-መዛሙርቱ፡ ወደእርሱ ቀርበው፣ የቤተ-መቅደሱን፡ የሕንጻ አሠራር ማማር እያዳነቁ ባሳዩት ጊዜ፣ **ወአውሥአ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ትሬእዩኑ፡ ዘንተ ኵሎ? አማን እብለክሙ! ኢይትኀደግ ዝየ፡ እብን፡ ዲበ እብን፡ ዘኢይትነሠት።** በውኑ፡ ይህን ኹሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ! ድንጋይ፡ በድንጋይ ላይ እየተገነባ የተሠራው ይህ ሕንጻ፡ በዚህ ሳይፈርስ አይቀርም።" በሚል ቃሉ፡ ለእነርሱ፣ ለሐዋርያቱም እንኳ ጭምር አስገንዝቧቸዋል። (ማቴ. ፳፩፥ ፲፪-፲፫። ማር. ፲፩፥ ፲፭-፲፯። ሉቃ. ፲፱፥ ፵፭-፵፮። ዮሐ፣ ፪፥ ፲፬-፳፪።)

ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚያ፡ በምሴተ-ሐሙስ የፋሲካ ገበታቸው ላይ የተናገረውንም ታውቃላችሁ፤ እሱም፡ እንዲህ በሚለው ቃሉ ከተናገረው በኋላ፣ በተግባር ፈጽሞ ያሳየው፡ መለኮታዊው እና ትስብእታዊው የምሥጢረ ሥጋዌው ትንግርት ነው፡- **"ወእንዘ ይበልዑ፡ ነሥአ ኅብስተ፡ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወባረከ ወፈተተ፤ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ፤ ወይቤሎሙ፡- 'እንክሙ ብልዑ፣ ዝ ውእቱ ሥጋየ። ወነሥአ ጽዋዐኒ፤ ወአእኰተ፤ ወወሀቦሙ፡ እንዘ ይብል፡- 'ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ፤ ዝ ውእቱ ደምየ፣ ዘሐዲስ ሥርዓት፣ ዘይትከዐው በእንተ ብዙኃን፣ ለኀድገተ-ኃጢአት።**

"ሲበሉም፣ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ፡ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፤ ቆራረሰውም፤ ለደቀ-መዛሙርቱም፡ እንዲህ እያለ ሰጣቸው፡- 'እንካችሁ! ብሉት! ይህ ሥጋዬ ነው። እንደዚሁም፡ የጽዋዉን ወይን አንሥቶ፡ ባረከው፤ እንዲህ እያለም ሰጣቸው፡- 'ከዚህ የጽዋ ወይን፡ ኹላችሁም ጠጡ! ይህ፡ ስለብዙዎች፡ ከኃጢአት መንጻት፡ አዲስ ሥርዓት ኾኖ የሚፈስስ፡ ደሜ ነው።" (ማቴ. ፳፮፥ ፲፯-፳፰። ማር. ፲፬፥ ፲፪-፳፭። ሉቃ. ፳፪፥ ፯-፳።)

**እንግዴህ፡ እስካኹን፡ ይህን እውነታ ያላወቃችሁ ካላችሁ፡ ዕወቁት! ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፣ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት፡ እናንተ ልጆቻችን፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን ያገኛችሁት፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ-አምልኳችሁ፡ ይህ፡ የጎብስተ-አኰቴት እና የጽዋዓ-በረከት ሥርዓተ-አምልኮ፡ ነውና።**

## አሪታዊው የአይሁድ የአምልኮ ወግ*፡-
## በደም የተበከለው፡
## የመሥዋዕታቸው እና የቍርባናቸው አቀራረብ ልማድ።

[*ወግ የተባለው፡ ለሥርዓትነት የማይበቃ በመኾኑ ነው።]

ደጉ እና የዋሁ፣ ቡሩኩ እና ምርጡ ልጃችን አቤል፡ ለእኛ ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት፡ **የጎብስተ-አኰቴቱ እና የጽዋዓ-በረከቱ ሥርዓተ-አምልኮ ፍሬ የኾነው፡** የስንዴው ነዶና የወይኑ ዘለላ ሊኾን በተገባ ነበር።

ይኸውም፡ ወላጆቹ፡ አዳም እና ሔዋን፣ በጥንታዊነት እና በመሠረታዊነት የጀመሩት፣ ኋላም፡ ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ እና ሳሌም የቀጠሉት፣ ከዚያም፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ እስከዛሬ አጽንተው ያኖሩት፣ በመጨረሻም፡ በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ መድኃኒትነት እና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ሰላመ-መስቀል ቤዛነት በተገኘው፡ በቅዱሱ ሥጋችን እና በክቡሩ ደማችን ቍርባን፡ የኪዳነ-ምሕረታችን መገለጫና ማኅተም ኾኖ፡ ለዘለዓለም የጸናው፣ እኛም እግዚአብሔር፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ ለምንጊዜውም፡ ወድደን የምንቀበለው፡ ይኸው፡ **የጎብስተ-አኰቴቱ እና የጽዋዓ-በረከቱ፡ የቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኮ** ነው።

አቤል ግን፡ ይህን ትቶ፡ ያቀረበልን መሥዋዕት፡ እኛ እግዚአብሔር የማንሻውን፣ እንዲያውም የምንጸየፈውን፣ ትዕቢተኛው ተገዳዳሪያችን ዲያብሎስ ግን፡ እጅግ የሚፈልገውን፣ የሚደሰትበትንም፡ የፍጡራችንን፥ የእንስሳውን ደም በማፍሰስ ኾነ።

ከዚህ የተነሣ፡ የአቤልን መሥዋዕት፡ ልንቀበለው ባልተገባ ነበር። ነገር ግን፡ ቀደም ብዬ እንዳሳወቅኋችሁ፡ "እኛ እግዚአብሔር፡ ምንጊዜም፡ ሊቀርብልን የምንወድደው፣ የምንቀበለውም <u>መሥዋዕት</u>፡ በምንነቱ ዓይነት ላይ የተመሠረተ እና ያተኰረ ሳይኾን፣ ምንም ምን ይኹን፡ ያን መሥዋዕት የምንቀበለው፡ ራሱ፡ የመሥዋዕቱ አቅራቢ፡ የሚያቀርብበት፡ የነፍሱ ሃይማኖታዊ እውነተኝነት እና የሥጋው ምግባራዊ ቅንነት፣ የመንፈሱም ባሕርያዊ ንጽሕና፡ ፍጹም ኾኖ ስናገኘው ብቻ በመኾኑ፣ አቤልም ለዚያ ማንነት እና ምንነት በቅቶ ስላገኘነው ተቀበልነው።

እኛ እግዚአብሔር፡ ምንም እንኳ፡ የአቤልን፡ መሥዋዕቱን፡ በዚያ ብቅዓቱ ምክንያት፡ ብንቀበለውም፡ የኋላ-ኋላ ግን፤ "አትግደል!" ከሚለው ትእዛዛችን ጋር፣ የቅድስት ሥላሴነት መንበረ-ጸባዖታችንን ከሚሸከሙት አርባዕቱ እንስሳ መካከል፡ አንዱ የኾነውን ሕያዉን በግ ዐርዶ በመግደል፡ ደሙን በማፍሰሱ፣ እርሱም፡ በወንድሙ በቃየል እጅ ተገድሎ፡ የእርሱም ደም፡ ሊፈስስ በቃ።

የዚህ፡ የአቤል፡ ነፍስ የመግደሉ እና ደም የማፍሰሱ ጥፋት ኃጢአት የሚሰረየው፡ በዚያው፡ በራሱ ደም መፍሰስ በመኾኑ ብቻ ነውና። ይኸውም፡ "**ወበደም ይነጽሕ ኵሉ፡ በሕገ ኦሪት፤ ወዘእንበለ ይትነዛኅሰ ደም፡ ኢይሰረይ።** በኦሪቱ ሕግ፡ ኹሉ ኃጢአት የሚነጻው፡ በደም ነው፤ ደም ሳይፈስ የሚሰረይ ኃጢአት የለም።" በሚለው፡ በኋለኛው የመጽሐፋችሁ ቃል መሠረት፡ ይህን፡ የኦሪታውያኑን አይሁድ ይትበሃል፡ ልትቀበሉት ይቻላችኋል። (ዘሌዋ. ፲፯፥ ፲፩። ዕብ. ፱፥ ፳፪።)

እንግዲህ፡ በዚህ መልክ እና ይዘት፡ ከአዳም እና ሔዋን አንሥቶ፡ በታማኞቹ አገልጋዮቻችን፡ በኖኅ እና በሓይከል አማካይነት፣ "ኢትዮጲስ" እስከተባለው፣ እስከሥዩሙ ልጃችን እና ካህናችን፣ የመንግሥታችንም አጼያዊ ተጠሪያችን እስከኾነው፡ እስከቀዳማዊው መልከ-ጼዴቅ፣ ከዚያም፡ "አቤሜሌክ" በተባለው፣ አብርሃምን በባረከው፡ በማእከላዊው መልከ-ጼዴቃችን ጽኑ ድልድይነት፡ "ኢየሱስ መሲሕ" እስከተባለው፣ የመጀመሪያውም፣ የመጨረሻውም፡ አንድ ልጃችን እስከኾነው፡ እስከአማናዊው መልከ-ጼዴቅ እግዚአብሔር ወልድ ድረስ የኖረው፣ በእርሱም ጸንቶ፡ ይኸው እስካኹንና ወደፊትም፡ በድል አድራጊነት ሊቀጥል የቻለው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ሥርዓት፡ በኅብስተ-አኰቴቱ እና በጽዋ-በረከቱ፡ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው፡ ይህ ዓይነቱ መሥዋዕት ነው።

ቃየል፡ በወንድሙ በአቤል አንጻር፡ ለእኛ ለፈጣሪው እግዚአብሔር፡ ያቀረበልን መሥዋዕት፡ በገበሬነቱ፡ ከምድር ፍሬ ያመረተውን ያንኑ፡ የወላጆቹን፡ የኅብስተ-አኰቴቱን እና የጽዋዓ-በረከቱን፡ የምስጋና ሥርዓት-አምልኮ የተከተለ እንደነበረ ዐውቃችሁታል። ነገር ግን፡ ይኸው ቃየል፡ በመሥዋዕት አቅራቢነቱ፡ ያቀረበበት፡ የራሱ፡ የነፍሱ ሃይማኖታዊ እውነተኛነት እና የሥጋው ምግባራዊ ቅንነት፣ የመንፈሱም ባሕርያዊ ንጽሕና፡ ፍጹም መኾኑ ቀርቶ፡ እንዲያውም፡ የእነዚህ የአቤሉ ሀብታት ተቃራኒ የኾኑት፣ የነፍሱ ሃይማኖታዊ ሓሳዊነት እና የሥጋው ምግባራዊ ጥመት፣ የመንፈሱም ባሕርያዊ ርኵሰት ገዝፈው እና ጎልተው የተከሠቱበት ኾኖ ስለተገኘ፡ መሥዋዕቱን፡ ሳንቀበለው ቀረ።

በዚህ የተነሣ፡ በወንድማማቹ መካከል፡ ጠላትነት ተፈጥሮ፡ ቃየል፡ በቂም በቀል ክፋት ተነሣሥቶ፡ የወንድሙን ደም በማፍሰስ፡ እስከመግደል ደረሰ። ይህም ጠንቅ፡ የቃየል ወገኖች በኾኑት፡ "የሰው ልጆች" እና የአቤል ወገኖች በኾኑት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" መካከል፡ ይኸው፡ እስከዛሬ ድረስ ጸንቶ፡ የጥላቻው ዘመቻ እና የጦርነቱ ፍጅት ሳይቋረጥ እንደቀጠለ ይታያል።

በቃየል ወገንነታቸው ምክንያት፡ "የሰው ልጆች" የተባሉት አይሁድ፡ ቃየል፡ ወንድሙን በመግደሉ፡ በሰይጣናዊነቱ ጸንቶ የቀጠለውን፡ የደም ማፍሰሱን የአምልኮ ወግ፡ እነርሱም፡ እስከአባታቸው አብርሃም እና እስከኦሪቱ ሕጋቸው ድረስ፡ በአረማዊነታቸው እና በጣዖት አምላኪነታቸው፡ የወለዷቸውን ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻቸውን ሳይቀር፡ ለዲያብሎስ እያረዱ፡ ደማቸውን፡ በመሥዋዕትነት በማቅረብ የኖሩበት መኾናቸው፡ ራሱ አብርሃም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ትምህርታዊ ቡራኬ፡ ለአምልኮተ-እግዚአብሔር እና ለቅዱሱ-ኪዳን ግርዛት እስከበቃበት ጊዜ ድረስ፡ የነበረበት ዝክረ-ነገሩ፡ አብራርቶ ያስረዳችኋል።

እኛ እግዚአብሔር፡ በሰፊው ለጋስነታችን፡ ላደረግንላቸው፡ ለዚያ ኹሉ ቸርነታችን፡ በምንም ሚዛን ሊበቁ ስላልቻሉት፤ እንዲያውም፡ ልጄ ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ያለፍርድ፡ በጭካኔ እስከመግደል ስለደረሱት፡ ስለኦሪታውያኑ አይሁድ፡ አንዱ፡ ኢትዮጵያዊው ነቢያችን፡ "'**አኮ ከመ ደቂቀ-ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፤ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፤ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።** 'የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።' አለ፤ ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር።" ብሎ፡ የተናገረባቸውን የእውነት ቃል፡ ኹሉም፤ እነርሱ ጭምር ያውቁታል። (አሞ. ፱፥ ፯።)

እነዚሁ፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር ነቢይ፡ እንዲህ ተብሎ የተነገረባቸው፡ ያለምክንያት አይደለም። አንዱም ምክንያት፡ እነዚሁ አይሁድ፡ የኢትዮጵያ ልጆች መታወቂያ የኾነውን፤ እኛም እግዚአብሔር፡ ደስ ብሎን የምንቀበለውን፡ **የኀብስተ-አኰቴቱን እና የጽዋዓ-በረከቱን፡ የቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኮ** መምረጥ ሲችሉ፤ ሲገባቸውም፤ ነገር ግን፡ እነዚሁ አይሁድ፡ ይህን ትተው፡ የመረጡት እና የተከተሉት ወግ፡ ይህንኑ፡ የእንስሳትንና የአዕዋፍን ሕይወት በመግደል፤ ደማቸውንም በማፍሰስ፡ በይፋ የታወቀውን እና በሰው ወገኖች ኹሉ ዘንድ፡ ተቀባይነትን ያገኘውን፡ ደም የማፍሰሱን ሰይጣናዊ የአምልኮ ልማድ ኾነ።

አዎን! እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆቻችን፡ በታማኞቹ አገልጋዮቻችን፡ በሙሴ እና በአማቹ፡ በኢትዮጵያዊው ዮቶር አማካይነት፡ ለእነዚሁ ለኦሪታውያኑ አይሁድ፡ በሚገባ አሳውቀው ያስረከቧቸውን፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን ሥርዓት፡** እነዚሁ ዐመፀኞቹ እና አንገተ-ዳንዳኖቹ አይሁድ፡ "እኛ፡ የአሕዛቡን እንጂ፡ ይኼኛውን፡ የእግዚአብሔሩን አንፈልገውም፤ ይቅርብን!" ብለው አሽቀንጥረው እንደጣሉት ኹሉ፤ አኹንም፡ በአምልኳቸው ረገድ፡ እነዚሁ አይሁድ፡ የመረጡት እና የተከተሉት ወጋቸው፡ ደም የማፍሰሱን ሰይጣናዊ የአምልኮ ልማድ ኾነ።

ይህ በመኾኑ "የሙሴ መጻሕፍት"፣ በተለይም፡ "ሰመንቱ ብሔረ-ኦሪት" በተባሉት፡- ኦሪት ዘልደት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኍልቍ፣ ኦሪት ዘዳግም፣ ኦሪት ዘኢያሱ፣ ኦሪት ዘመሳፍንት፣ ኦሪት ዘሩት፣ በአጠቃላይም፡ በብሉይ ኪዳኑ በተካተቱት መጻሕፍት ውስጥ፡ ይኸው፡ ደም የማፍሰሱ ሰይጣናዊ የአምልኮ ልማዳቸው፡ የእኛ የእግዚአብሔር ሕግ እንደኾነ ተደርጎ ቀርቦ፡ ለአንዴ እና ለመቼውም ጊዜ ጸንቶ ሊቀጥል የሚችልበትን ሙከራቸውን ሠዉ። ነገር ግን፡ አልቻሉም፤ አይችሉምም።

በመጨረሻ፡ እኛ እግዚአብሔር ስንጸየፈው የቆየው፣ ታማኞቻችን የኢትዮጵያ ልጆችም፡ ከጥንቱም ቢኾን የማያውቁት፣ እንደርኵሰትም የሚቆጥሩት፡ ይኼው፡ ደም የማፍሰሱ የአይሁድ፡ ሰይጣናዊ የአምልኮ ልማዳቸው፡ በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ መድኃኒትነት እና በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ሰላመ-መስቀል ቤዛነት በተገኘው፡ በቅዱሱ ሥጋችን እና በክቡሩ ደማችን ቍርባን፡ የኪዳነ-ምሕረታችን መገለጫና ማኅተም ኾኖ፡ ለዘለዓለም በጸናው፣ እኛም እግዚአብሔር፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ ለምንጊዜውም፣ ወድደን በምንቀበለው፡ በዚህ፡ በኢትዮጵያዊው ኅብስተ-አኰቴት እና ጽዋዓ-በረከት በሚፈጸመው፡ የቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኮ እነሆ፡ ለዘለዓለም ተሻረ።

በእርሱም ቦታ፡ ያው፡ በኢትዮጵያው ኅብስተ-አኰቴት እና ጽዋዓ-በረከት የሚፈጸመው፡ ጥንታዊው እና ቀዳማዊው፡ የቅዱስ ቍርባኑ እና የምስጋናው ሥርዓተ-አምልኮ ወደነበረበት ተመልሶ፡ ተተካ።

ይህንም እውነታ፡ ትጉሁ ሓዋርያችን ጳውሎስ፡ ወደእነዚሁ፡ "ዕብራውያን" ወደሚባሉት አይሁድ፡ እንዲህ ሲል የጻፈላቸው ቃል፡ በበለጠ ያስረዳችኋል፡-

"እስመ ጽላሎታ ይእቲ ኦሪት፡ ለእንተ ትመጽእ ሠናይት፤ እስመ ኢኮነት ለሊሃ። ወበእንተ ዝንቱ፡ አመ ያበውኡ መሥዋዕተ ዘልፈ፡ በኵሉ ዓመት፡ <u>ኢይክል ለሊሁ ግሙራ ፈጽሞ ለእለ ያበውእዎ።</u> ወእመ አኮሰ እምአዕረፉ፡ እምዘ ይሠውዑ፣ እስመ ይሠሪ ሎሙ ኃጢአቶሙ፡ ለእለ ይሠውዑ፤ ወያነጽሖሙ በምዕር።

"አላ ዳዕሙ ቦሙ፡ ዘይገብሩ ተዝካረ ኃጢአት በበዓመት፣ በውእቱ መሥዋዕት። <u>እስመ ኢይክል ደመ-ላሕም፣ ወጠሊ፡ ይኅድግ ኃጢአተ።</u> ወበእንተዝ፡ አመ ይመጽእ ውስተ ዓለም፡ ይቤ፡- <u>'መሥዋዕተ፥ ወቍርባነ ኢፈቀድከ!</u> አላ አልበስከኒ ሥጋ። <u>መሥዋዕተ፡ ዘበእንተ ኃጢአት ኢሠመርከ።</u> ውእተ ጊዜ እቤ፡- 'ነየ መጻእኩ፤ ውስተ ርእሰ መጽሓፍ፡ ተጽሕፈ በእንቲአየ፣ ከመ እግበር ፈቃደከ፡ መከርኩ አምላኪየ። መልዕልቶ፡ ይቤ፡- <u>'መሥዋዕተ፥ ወቍርባነ ኢፈቀድኩ! ዘበእንተ ኃጢአት ኢሠመርኩ፡ ዘይሠውዑ በሕገ ኦሪት</u> ብሂሎ።

"ወእምዝ፡ ይቤ፡- 'ነየ መጻእኩ፡ ከመ እግበር ፈቃደከ አምላኪየ።' ወዝ ቃል፡ ይነሥት ቀዳማየ፤ ከመ ያቅም ደኃራየ፤ ከመ ንትቀደስ በሥምረቱ፤ በቍርባነ ሥጋሁ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፤ ዘኮነ በምዕር። ወኵሉ ሊቀ-ካህናት፡ ይቀውም ኵሎ አሚረ፤ ወይሠውዕ ኪያሃ፡ ከመ መሥዋዕት፡ እንተ ለግሙራ፡ኢትክል አንጽሖ ኃጢአት። ወውእቱሰ [እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ]፡ ምዕረ ሦዐ፡ መሥዋዕተ፡ እንተ ለዝሉፉ፤ በእንተ ኃጢአትነ፤ ወነበረ በየማነ እግዚአብሔር።

"ኦሪት [ሕግ]፡ ልትመጣ ላላት መልካም ነገር፡ የነገር ጥላ ናት እንጂ፣ እውነተኛ አምሳል አይደለችምና። ስለዚህም፡ በየዓመቱ፡ ዘወትር የሚያቀርቡት፡ ያ፡ የኦሪቱ መሥዋዕት፡ በራሱ፡ መሥዋዕቱ የቀረበላቸውን ሰዎች ኃጢአት፡ ሊያስተሰርይላቸው ፈጽሞ አይችልም። እንደዚህማ ባይኾን ኖሮ፡ በአንድ ጊዜ ባቀረቡት መሥዋዕታቸው፡ ኃጢአታቸው ተሰርዮላቸው የሚያነጻቸው ስለሚኾን፡ ከዚያ በኋላ፡ በየጊዜው ከመሠዋት ባረፉ ነበር።

"ነገር ግን፡ በዚያ መሥዋዕት፡ በየዓመቱ፡ የሚያደርጉት የኃጢአት መታሰቢያ አላቸው። በየጊዜው የሚፈስሰው፡ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም፡ ኃጢአትን ሊያስወግድ፡ ከቶ የማይችል ነውና። ስለዚህ፡ [እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ] ወደዓለም በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡- [በኦሪቱ ወግ የሚቀርብልህን] 'መሥዋዕቱን እና ቍርባኑን ስላልወደድህ፤ ሥጋን አለበስኸኝ። ስለኃጢአት የሚቀርበው መሥዋዕት፡ አላስደሰተህም። በዚህ ጊዜ፡ 'ስለእኔ፡ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ እንደተጻፈው፡ ‹አምላኬ ሆይ! ፈቃድህን ልፈጽም፡ እነሆ፡ እኔ፡ ወስኜ መጥቻለሁ!› አልሁ።' ከዚህም በላይ፡ 'እንደኦሪቱ ሕግ፡ ስለኃጢአት ማስተስረያ እያሉ የሚያቀርቡትን፡ መሥዋዕቱን እና ቍርባኑን አልፈቀድሁትም፤ አልወደድሁትምም!' ብሎ ተናገረ።

"ቀጥሎ፡ 'አምላኬ ሆይ! ፈቃድህን ላደርግ፡ እነሆ መጥቻለሁ!' አለ። ይህም ቃል፡ የኋለኛውን ሊያቆም፤ የፊተኛውን ይሽራል። አዎን! እግዚአብሔር፡ ወድዶ በተቀበለው፤ ለአንዴ እና ለዘለዓለምም በቀረበው፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ የሥጋ ወደሙ ቍርባን ተቀድሰናል። [የኦሪቱ] ሊቀ-ካህናት ኹሉ፡ ኃጢአትን ለማንጻት፡ ፈጽማ ያልተቻላትን፡ ያችኑ የተለመደችውን ደም የሚፈስስባትን መሥዋዕት ሊሠዋ፡ ኹልጊዜ በአገልግሎቱ ይቆማል። እርሱ [እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ] ግን፡ ስለኃጢአታችን፡ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ፡ ራሱን፡ የዘለዓለም መሥዋዕት አድርጎ ሠውቶ፤ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ።"

በዚህ ረገድ፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ዐልፎ፤ የዓለሙን ሃይማኖታውያን እና ሃይማኖታውያት ብቻ ሳይኾን፡ "አሕዛብ እና አረማውያን" የተባሉትን ሳይቀር ያስደመመ ነገር አለ።

ይኸውም፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" ብላችሁ የምትጠሩ ወገኖች ኹኔታ ነው። ያም፡ የእኛ "የእግዚአብሔር ልጆች!"፣ የእኔም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" የተባለችሁባቸው፣ ከዚህ የተነሣም፡ በመላው ዓለም ካሉት፣ ከሌሎቹ የሰው ወገኖች ከኾኑት ፍጡሮቻችን ኹሉ ተለይታችሁ፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችሁ መታወቂያዎች የኾኑላችሁን፡ መለኮታውያት ሥርዓቶቻችሁን ትታችሁ፣ ወይም አቃልላችሁ፥ ወይም ንቃችሁ፣ የኦሪታውያኑ አይሁድ የኾነውን፣ እነዚሁ አይሁድ፡ የመረጡትን እና የተከተሉትን፡ ሰይጣናዊ የኾነውን ልማድ፡ እናንተም እንደነርሱ መርጣችሁና ተከትላችሁ እየፈጸማችሁ ስትኖሩበት መታየታችሁ ነው።

ይኼንን፡ በኅብስተ-አኰቴት እና በጽዋዓ-በረከት፡ የሚፈጸመውን፣ ኢትዮጵያዊዉን፡ የቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኳችሁን ትታችሁ፣ ወይም አቃልላችሁ፥ ወይም ንቃችሁ፣ የኦሪታውያኑ አይሁድ የኾነውን፡ ደም የማፍሰሱን፡ ሰይጣናዊ የአምልኮ ልማዳቸውን፡ እናንተም እንደነርሱ መርጣችሁና ተከትላችሁ እየፈጸማችሁ ስትኖሩበት መታየታችሁ፡ በቂ ምስክሮች ሊኾኑ ከሚችሉ፡ ከብዙዎች ማስረጃዎች መካከል፡ ለዓይነት ያህል፡ የቅርብ ምርጫ ኾኖ ሊቀርብ ችሏል።

ይህም፡ <u>በመስከረም ፩ ቀን፣</u> የዕንቍጣጣሽ እና በትንሣኤ እሑድ የፋሲካ በዓሎቻችሁ፣ በእነዚህ ኹለት የበዓላት ዕለታት፡ በኢትዮጵያውያን እና በኢትዮጵያውያት ዘንድ እና መካከል፡ በየዓመቱ የሚታየው እና የሚፈጸመው ጠቅላላ፡ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ፥ ግላዊ እና ቤተሰባዊ፣ ማኅበራዊ እና ብሔራዊ የዝግጅት እና የመሰናዶ፣ ግርግር እና ትርምስ፣ ሽርጉድ እና ውጣውረድ፡ ለምስክርነትና ማስረጃነት ለቀረበው፡ ለዚሁ የቅርብ ምርጫ፡ ሰፊ መድረክ ኾኖ፡ ጭብጥ ኹኔታዎችን አጉልቶ ሊያሳይ፣ አብራርቶም ሊያስረዳ የተመቸ እና የበቃ ኾኗል።

እነዚህ፡ ኹለት የበዓላት ዕለታት፡ ፩ኛው፡ የእኔ የእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰውነት ወደዚህ ዓለም መጥተን የተገለጥንበት፡ የልደታችን መታሰቢያ ዕለት፣ ለእናንተ የአዲስ ዘመን ዐውደ-ዓመት በዓላችሁ የኾነው፡ <u>መስከረም ፩ ቀን</u>፣ ነው፤ ፪ኛዋ ደግሞ፡ ልጇ ወዳጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከሕማማተ-መስቀሉ ሞት እና መቃብሩ በኋላ፡ በድል-አድራጊነቱ ያስገኘው፡ የትንሣኤው መታሰቢያ በዓላችሁ የሚውልባት፡ "ሰንበት ዝልፍት" የኾነችው፡ የሚያዝያ ፩ ቀኗ እሑድ ናት።

እንግዴህ፡ እየራሳችሁ ፍረዱ! ይኼ ኹሉ፡ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ፥ ግላዊ እና ቤተሰባዊ፣ ማኅበራዊ እና ብሔራዊ የዝግጅት እና የመሰናዶ፣ ግርግርና ትርምስ፣ ሽርጉድ እና ውጣውረድ፡ ከቶ ለምንድር ነው? በኅብስተ-አኰቴት እና በጽዋዓ-በረከት፡ ስለሚፈጸመው፣ ስለኢትዮጵያዊው፡ የቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኳችሁ መልካም ክዋኔ ተብሎ ነውን?

ወይስ፡ የኦሪታውያኑ አይሁድ የኾነውን፡ ደም የማፍሰሱን፡ ሰይጣናዊ የአምልኮ ልማድ፡ በተሟላ ተግባር ላይ ለማዋል የሚፈጸም ጥረት እና ድካም ነው? በማስተዋል ተመልከቱት! ኹላችሁ የምታውቁትን፡ ገሃድ እውነታም፡ ደግሜ ልግለጥላችሁ!

የእኛ የእግዚአብሔር የልደታት ዕለት በዓል በኾነው፡ በመስከረም ፩ ቀን፥ የሚደረገውን ኹሉ ታውቁት የለምን? በኅብስተ-እኰቴት እና በጽዋዓ-በረከት ሥርዓተ-አምልኮ መሠረት፡ የእኛ የእግዚአብሔር መሥዋዕት እና ቍርባን ኾኖ የቀረበውን፡ ቅዱሱን ሥጋችንን እና ክቡሩን ደማችንን፡ በየቤተ-ክርስቲያናችሁ፥ ወይም፡ በእየቤታችሁ ተቀብላችሁ፡ ያንን በመብላት እና በመጠጣት ፈንታ፣ አዎን! ይህንኑ በዓላችሁን፡ በእግዚአብሔር እውነት እና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ፡ እንዲህ በማክበር፡ እውነተኛ ማንነታችሁን እና ምንነታችሁን በማረጋገጥ ፈንታ፣ እናንተ እያደረጋችሁ ያላችሁት፡ ከቶ ምንድር ነው?

ባዕዳኑ ፈረንጆች፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ እና በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቀንደኛ መሪነት፡ ይህን የእኛን፡ የእግዚአብሔርን የልደታት ቀን፡ የጣዖቶቻቸው የበዓል ቀን ወደኾነው፡ ወደታኅሣሥ ፳፰፥ ወይም፡ ፳፱ ቀን ማዘዋወራቸውን መቀበላችሁ ሳያንስ፣ በዚያው፡ በእኛው የልደታት ቀን፡ በየቤታችሁ የምትፈጽሙት ግብር፡ አዎን! ምንድር ነው? "ነጭ እና ጥቁር፣ ቀይ እና ገብስማ" እየተባለ፣ የመልኩም ቀለም ተለይቶ እየተመለከተ፡ በአምልኮ-ባዕድ ልማድ፡ ለእርድ የሚቀርበውን የዶሮ እና የእንስሳት ዓይነት በማዘጋጀት፡ የኦሪታውያኑ አይሁድ የኾነው፡ ደም የማፍሰሱ፡ ሰይጣናዊ የአምልኮ ወግ፡ በታላቅ አክብሮት እና ትጋት፣ ጥንቃቄ እና ኅብረት እንዲካኼድ እየተደረገ አይደለምን? ይህን ትክዳላችሁን? ለእኛ ለእግዚአብሔር፡ ልትክዱ አትደፍሩም።

በልጄ፣ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ የትንሣኤ በዓሉ ዕለት የምትፈጽሙት ድርጊት፡ ይህንኑ የመሰለ ነው። የሑዳዴ፥ ወይም፡ የአርባ ቀን ጾማችሁንና የሕማማተ-መስቀሉን ሳምንት፡ በስግደት እና በአክፍሎት ከጨረሳችሁ በኋላ፣ በትንሣኤው ሌሊት፡ በኅብስተ-እኰቴት እና በጽዋዓ-በረከት ሥርዓተ-አምልኳችሁ መሠረት፡ የእኛ የእግዚአብሔር መሥዋዕት እና ቍርባን ኾኖ፡ በየቤተ-ክርስቲያናችሁ የቀረበላችሁን፡ የቅዱሱ ሥጋችንን እና የክቡሩ ደማችንን ማዕድ ተቀብላችሁ፡ ያንን በመብላት እና በመጠጣት ፈንታ፣ ይህንኑ የትንሣኤ በዓላችሁን፡ በእግዚአብሔር እውነት እና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ፡ እንዲህ በማክበር፡ እውነተኛ ማንነታችሁን እና ምንነታችሁን በማረጋገጥ ፈንታ፣ እናንተ እያደረጋችሁ ያላችሁት፡ ከቶ ምንድር ነው?

በዚያች፡ በትንሣኤዋ ሌሊት፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር በቀረበላችሁ ማዕድ ላይ ተገኝታችሁ፡ የመሥዋዕትነት ቁርባናችን የኾነውን፡ ቅዱሱን ሥጋችንን እና ክቡሩን ደማችንን፡ በመሳተፍ ፈንታ፣ በየቤታችሁ ተመልሳችሁ፡ የምታደርጉትን ልንገራችሁ!

በእነዚያ፡ በሃምሳ ስድስቱ የጾም እና የጸሎት፣ የስግደት እና የአክፍሎት ቀኖች ያዘጋጃችሁትን፡ የዶሮ እና የእንስሳ ሥጋ ምግብ፣ የመጠጥም ዓይነት በማቅረብ፣ ያንንም ድግሣችሁን፡ በታላቅ ተድላ ደስታ፡ በመብላት እና በመጠጣት፡ የፋሲካ በዓላችሁን ማክበር ነው። ይኼም በዓላች የተመሠረተው እና ያተኰረው፡ የኦሪታውያኑ አይሁድ በኾነው፡ በደም ማፍሰሱ፡ ሰይጣናዊው የአምልኮ ልማድ ላይ መኾኑን ይመሰክርባችኋል።

በዚህ ኹሉ የጥፋት ግብር፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ቅዱስ** ኪዳን ላይ፡ በመተባበር በፈጸሙት፡ በክህደቱ እና በዓመፁ፥ በአምልኮ አመንዝራነቱ እና በክፋቱ ኃጢአታቸው ምክንያት፡ በእኛ በእግዚአብሔሩ መለኮታዊ የውግዘት ቀንበር ሥር፡ በአንገተ-ደንዳናነት እየማቀቁ ያሉት ቤተ-ሕዝቡ እና ቤተ-ምልክናው ብቻ ሳይኾኑ፡ ቤተ-ክህነቱ ጭምር፣ ካህናቱን ይዞ፡ በግንባር ቀደምትነት ተጠያቂዎች ናቸው።

በስሜ የተጠራችሁ፡ እናንተ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ወደኋላ ባለው ዜና መዋዕላችሁ፣ ዛሬም፡ በዚህ በምትገኙበት ዘመን ሳይቀር፡ እርስ-በርሳችሁ፡ ውስጥ-ውስጡን እየተናቆራችሁ እና እየተፋጃችሁ ቆይታችሁ፡ በመጨረሻ፡ በምታደርጉት ጦርነት፡ እንዲህ፡ የደም መፋሰሱ ዕልቂት የቀጠለው፡ ታዲያ! በምን ምክንያት ይመስላችኋል? ከዚሁ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ከኾነው፡ ከኢትዮጵያዊው፡ **የኀብስተ-አኰቴት እና የጽዋዓ-በረከት፡** ቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኳችሁ ይልቅ፡ የዲያብሎስ የኾነውን የኦሪታውያኑን አይሁድ፡ የደም ማፍሰሱን፡ ሰይጣናዊው የአምልኮ ልማድ በመምረጣችሁ መኾኑን፡ እንዴት ማስተዋል አቃታችሁ? ከመለኮታዊው ውግዘት ልትፈቱ የሚያስችላችሁን ንስሓ፡ በጊዜው እና በአግባቡ ለመፈጸም፡ እኹንም፡ በእንቢተኝነት ዕልሃችሁ መቀጠልን ስለመረጣችሁ፣ ይህን እውነታ ለማስተዋል፡ ዓቅሙን አጣችሁ።

ስለዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በፈጸማችሁት፡ በክህደቱ እና በዓመፁ፥ በአምልኮ አመንዝራነቱ እና በክፋቱ ኃጢአታችሁ ምክንያት፡ ከታሠራችሁበት፡ ከከባዱ መለኮታዊ የውግዘት ቀንበር ተፈትታችሁ፡ መልካሟን የኪዳነ-ምሕረት ሕይወት ለመኖር ይቻላችሁ ዘንድ፡ በኹሉም አኳያ፡ እኛ እግዚአብሔር ወደምናውቀው እና ወደምንቀበለው፡ ወደቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ ሥርዓተ-አምልኮና ምግባር፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ ትመለሱ ዘንድ፡ በእናትነት ፍቅሬ ልጆቼን ኹሉ አሳስባችኋለሁ።

እንግዲህ፡ የቃየልን እና የአቤልን የመሥዋዕት አቀራረብ መልክ እና ይዘት፡ መነሻ በማድረግ፡ እስካኹን ያሳወቅኋችሁን እውነታ፡ በዚሁ ላብቃ! ይህም እውነታ፡ በአንድ ወገን፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ደስ ብሎን ስለምንቀበለው፡ ስለኢትዮጵያዊው፡ **የኀብስተ-አኰቴት እና የጽዋዓ-በረከት፡ ቅዱስ ቍርባን እና የምስጋና ሥርዓተ-አምልኮ** የተብራራው ነው።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ "በኦሪቱ ሊቀ-ካህናት፡ በየጊዜው የሚፈስሰው፡ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም፡ ኃጢአትን ሊያስወግድ፡ ከቶ የማይችል በመኾኑ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ፡ 'በኦሪቱ ወግ የሚቀርብልህን፡ መሥዋዕቱን እና ቊርባኑን ስላልወደድህ፤ ሥጋን አለበስኸኝ!' ብሎ፤ ስለሰዎች ኃጢኣት፡ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ፡ ራሱን፡ የዘለዓለም መሥዋዕት አድርጎ ሠውቶ፤ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ።" ተብሎ ስለተጻፈበት፤ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ለመሥዋዕት፡ ደም ስለሚያፈስሱበት፡ ስለሰይጣናዊው የአምልኮ ልማድ የታተተው ነው።

አኹን ደግሞ፡ በዚሁ የዐዋጅ ቃሌ ላስሰማችሁ የፈለግኋቸውን፡ ሌሎቹን ጥቂቶች ነገሮች አስከትልልላችኋለሁ። እነዚህም፡ ከጀመርነው፡ ከ፩ኛው ተራ ቊጥር የሚቀጥሉ ናቸው።

፪. የዘለዓለም እናታችሁ የኾንሁት እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ "ወለተ ኢያቄም፥ ወሐና"፤ የዘለዓለም አባታችሁ የኾነው ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕም፡ "ወልደ-አብ፥ ወልደ-ማርያም" በሚል ስያሜ እንደምንጠራ ኹሉ፡ እናንተም፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እንዲሁ፡ ከእየራሳችሁ መጠሪያ ስማችሁ ቀጥሎ የምትጠሩበት መለያ መታወቂያችሁ፡ የወንድ ወላጃችሁን ስም ብቻ ሳይኾን፤ የሴቲቱ ወላጃችሁንም ስም ጭምር በተቀጣይነት የያዘ ኾኖ ሊነገርና ሊጻፍ ይገባል።

በነፍስ፥ በሥጋ እና በመንፈስ ተሟልቶ የደረጀው የሰውነት አካላችሁ፡ ለፍሬያማነት በቅቶ ያገኛችሁት እኮ፡ ከወንዱ ወላጃችሁ ቅንጣት ዘር ብቻ ሳይኾን፡ በእኩልነት፡ ከሴት ወላጃችሁ የደም አበባም ጭምር የተፈጠራችሁ በመኾናችሁ ነው።

ሴቲቱ ወላጃችሁ፡ ከፅንስ፡ እስከሽልነት፤ ከዚያም፡ እስከሰፋድል ሙሉ ሕፃንነት፡ በማሕፀኗ ተሸክማ፤ በእንግዴህ-ልጅ አማካይነትም፡ መግባ፤ የወለደች፤ ያጠባች እና አንከባክባ ያሳደገች፤ ከወንዱ ባለአደራችን ወላጃችሁ ጋር፡ የእኛ የእግዚአብሔር፡ ዋነኛዋ ባለአደራችን፡ ሴቲቱ ወላጃችሁ፡ በመኾኗ፡ አዎን! ሲኾን፡ ከዚያ በላቀ፤ ያ ካልኾነ ደግሞ፡ ቢያንስ፤ ቢያንስ፡ በወንድ ወላጃችሁ ስም ብቻ ሳይኾን፤ በሴቲቱ ወላጃችሁ ስም ጭምር መጠራት ይኖርባችኋል፤ ይገባችኋልም።

ስለዚህ፡ በዚህ፡ የየስማችሁ አጠራር፡ ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊነታችሁን አረጋግጣችሁ ለማሳወቅ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ይህን መመሪያ ሥርዓታችንን እንድትከተሉ አሳስባችኋለሁ። ከዚህ የተነሣ፡ የአንተ፡ የካህኑ ልጃችን፡ የኤርምያስ ስም አጠራር እና አጻጻፍ፡ "'ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ።' ይኾናል" ማለት ነው።

፫. በእናንተ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆቼ ዘመን አቆጣጠር፡ የ፯ሺ፭፻፱ ዓመታት ዕድሜ ባለው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ጥንታዊ ሥርዓት፡ በድንግልናቸው ጸንተው መቀጠልን ለሚመርጡት፡ ኢትዮጵያውያት ንግሥታት፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር፡ ጃንደረባ እንደሚመደብላቸው ኹሉ፣ እኔም፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በምድራዊው የህልውና ዘመኔ፡ የዚችው መንግሥታችን የሰማይ እና የምድር ንግሥተ-ንግሥታት፥ ወነገሥታት በመኾኔ፡ ጻድቁ ኢትዮጵያዊ ዮሴፍ፡ ለእኔ፡ ጃንደረባዬ ኾኖ፡ እኔን እና ሕፃኑ ልጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ እንዲያገለግለን ተመድቦልን እንደነበረ ዐውቃችኋል።

ልጄ እና እኔ፡ በመልከ-ጼዴቃ የኢየሩሳሌም ከተማ በነበርንበት ጊዜ፡ የምድራዊቷ ኢትዮጵያ፡ አጼዪት ለነበረችው፡ ለንግሥት ሕንደቄ፡ ጃንደረባ ኾኖ የተመደበው፡ ጻድቅ ሰው ደግሞ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" እየተባለ የሚጠራው፡ ሌላው ኢትዮጵያዊ ነበር። እርሱም፡ "እንደብሉይ ኪዳኑ፡ 'ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ' ኹሉ፡ "የአዲስ ኪዳኑ 'ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ' የሚባለው ነው።፣ በአንዳንድ ጸሓፊዎችም ዘንድ፡ "ባኮስ"፣ ይባላል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ከባለቃል-ኪዳን ታማኙ ልጃችን፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከሰሎሞን፡ የቅዱሱን ኪዳን ዘር፡ በድንግልናዋ ተቀብላ፡ የእኔ፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የልጄ የወዳጄ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ምዝላት የኾነውን፡ ቀዳማዊ ምኒልክን የወለደችው፡ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ የማክዳ "ጃንደረባ"፣ ኢትዮጵያዊው ጻድቅ፡ *"ታምሪን"* መኾኑን እንድታውቁት ይኹን።

እርሷው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ከታቀደው፡ የኢየሩሳሌም ጉዞዋ አስቀድማ፡ ወደእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን የላከችው፡ ይኸው፡ የንግሥት ማክዳ "ጃንደረባ" የኾነው፡ ኢትዮጵያዊው ጻድቅ፡ ታምሪን፣ በፀረ-ኢትዮጵያዊነታቸው በታውቁት፡ በኦሪታውያኑ የአይሁድ ካህናት እና በኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅ መነኮሳት ጳጳሳት ዘንድ፡ በ"ነጋዴነት" ተሰይሞ፡ በዚሁ፡ የፈጠራ ሙያው፡ ባለዝና ኾኖ ሲጠራበት እንደቆየ፡ ለኹላችሁም ግልጽ ነው። (፩ ነገ. ፲፥ ፩-፲፫። ኤር. ፴፰፥ ፯-፲፫። ማቴ. ፲፪፥ ፵፪። የሐዋ. ፰፥ ፳፯-፴፱።)

፬. "ኢትዮጵያዊነት"፡ ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ህላዌ እና ስም፣ አካልና ግብርም ስለኾነ፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ! ኢትዮጵያዊት ነኝ!" ብላችሁ፡ ለእየራሳችሁ፡ ስታስገነዝቡም ኾነ፣ ወይም፡ ለሌላው፡ ስታስተዋውቁ፣ ስለኹለት ቍም-ነገሮች፡ ለይታችሁ ማሳውቃችሁ እና ማመልከታችሁ ነው። እነዚህም ቍም-ነገሮች፡-

**<u>አንደኛው፥</u>** እናንተ፡ በእየግላችሁም ኾነ፡ በጋራ፡ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉት፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር የፍጥረት ወገኖች፡ አባሎች መኾናችሁን፡ ለይታችሁ የማሳውቃችሁ እውነታ ነው።

**<u>ኹለተኛው፥</u>** በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ የተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ እና ምግባራችሁ፣ ሕይወታችሁ እና ዜግነታችሁ፣ የህልውና-አቋማችሁ እና የኑሮ-ሥርዓታችሁ፣ በጠቅላላ ምንነታችሁ እና ማንነታችሁ፡ <u>በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ የተመሠረተ እና የሚመራ መኾኑን፣</u> ለይታችሁ የማመልከታችሁ እውነታ ነው።

"**ኪዳናዊ**" እና "**ኪዳናዊት**" የሚሉት ቅጽል ቃላት፡ የዚህ ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ እውነተኛነት ማጠናከሪያዎች እና ማረጋገጫዎች መኾናቸውን የተረዳችሁት ነው።

፫. በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ተዘጋጅቶና ተጽፎ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፣ በቁጥር ፲፩/፳፻፰ በወጣው የዐዋጅ ቃሌ ውስጥ፡ በስሜ በተጠራችው፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ የአኹኑ አገዛዝ ጠቅላይ ምሉክ የኾነውን፡ የኃይለ-ማርያም ደሳለኝን ስም፣ "ደሳለኝ ኃይለ-ማርያም" ብዬ መናገሬን፡ አንተ ኤርምያስ፡ በአንተ በኩል የተፈጸመ ስሕተት መስሎህ፡ ዐርመህ ልታስተካክለው መሞከርህን በማወቄ፣ ወዲያው፡ "ስሙን በሚመለከት የተናገርሁት፡ ትክክል ስለኾነ፡ የማስተካከል ሙከራህን እንድትተው፡ ከተግሣጼ ጋር ዐሳውቄህ፡ ይህንኑ ቃሌን መፈጸምህ ይታወስሃል።

በዚህ ረገድ፡ በጊዜው፡ ለአንተም ነግሬህ የነበረውን፡ አኹን፡ ለኹሉ ዐሳውቃለሁ። ይኸውም፡ የኃይለ-ማርያም ደሳለኝን ስም፣ "ደሳለኝ ኃይለ-ማርያም" ብዬ የተናገርሁት፡ ያለውን እውነተኛ ኹኔታ፡ በትክክል ለመግለጽ፡ ኾነ ብዬ ነው። አዎን! በአኹኑ ጊዜ ያለው እውነተኛ ኹኔታ፡ "ደሳለኝ ኃይለ-ማርያም" የሚለው፡ የስሙ ትክክለኛ መልእክት እንደተጠበቀ ኾኖ፡ ለዚያ ሕፃን ልጁ፣ ነገር ግን፡ ለዛሬው ፀረ-ማርያም ልጁ፡ "ኃይለ-ማርያም" ብሎ ስመ-ክርስትና የሰጠው፣ ይህንኑ የጥምቀት ስሙንም፡ የዓለም-ስሙ መጠሪያው ኾኖ እንዲቀጥል ያደረገው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮው የሚያምንብኝ፡ ታማኙ ልጄ የኾነው፡ "ደሳለኝ" መኾኑን ለመግለጥ ብዬ ነው። እርሱም፡ በስሜ በተጠራችው፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ የዛሬው አገዛዝ፡ ጠቅላይ ምሉክ የኾነው፡ የኃይለ-ማርያም ደሳለኝ ወንድ ወላጅ ነው።

፮.  እንደዚሁ ኹሉ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ተዘጋጅቶና ተጽፎ፡ በሚያዝያ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፣ በቁጥር ፲፱/፳፻፰ በወጣው ዐዋጅ ውስጥ፡ በገጾች ፺፫ እና ፺፯ ላይ፡ በስሕተት፡ ዮሓ. ፩ ተብሎ የተጻፈው ጥቅስ፡ ዮሓ. ፲፩ ተብሎ እንዲነበብ ይኹን! ስሕተቱ የደረሰው፡ ከአንተ፡ ከኤርምያስ ጥንቃቄ ጉድለት ሳይኾን፣ የሰው መሣሪያ የኾነው መቀመሪያ፡ የራሱ ሕፁፅነት ባስከተለው ቀውስ መኾኑ ይታወቅ።

፯. ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ከኾኑት እና ከሚባሉት ታማኞች ልጆቻችን እና ነጋሚዎቻችን፣ አገልጋዮቻችንና ዜጎቻችን ጀምራችሁ፡ አኹን እስካላችሁት ድረስ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በምትኖሩት መልካም የገነት ሕይወት፡ አዘጋጅታችሁ፣ እኛም እግዚአብሔር ተቀብለንላችሁ ዘወትር የምትደግሟቸውን አራቱን መደበኛ ጸሎቶቻችሁን፡ በሚገባ ታውቋቸዋላችሁ። እነርሱም፡- የእየራሳችሁ የኾኑት፡ የሃይማኖት እና የቃል-ኪዳን፣ ለእኛ የምታቀርቧቸውም፡ የምስጋና እና የሰላምታ ጸሎታት ናቸው።

እነዚህን ጸሎቶች፡ "አንተ ኤርምያስ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ በገለጽንልህ እና ባሳወቅንህ፡ በራስህ እንደምትጸልያቸው ኾነው እንዲገኙ፡ ተጠንቀቅበት!" ብዬህ፡ "እንዳለፉት ጊዜያት፡ አኹንም፡ ይህንኑ ጥንቃቄ ለማረጋገጥ፡ በአንቺው የዐዋጅ ቃልሽ፡ እንዲሰሰማ ብታደርጊልን፡ ለኹላችንም ይበጀናል!" ስላልኸኝ፡ በግእዙ ብቻ ሳይኾን፣ በኢትዮጵያኛው ጭምር የተሰናዳው፡ የአራቱ ጸሎታት ዝግጅት፡ ይኸው፡ አኹን፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በእኔው አንደበት እንድትሰሙት ፈቃዴ ኾኗልና፡ አዳምጡት! እንደተለመደው፡ ባዕዳኑም ያውቁት ዘንድ፡ በእንግሊዝኛው ሳይቀር የተሰናዳው ትርጉም፡ ዐብሮ ቀርቧል።

## ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያ።

ንሕነ፡ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡-

ነአምን፡ በአሓዱ አምላክ፤ እግዚአብሔር ጸባዖት፤ አኀዜ ኵሉ፤ ገባሬ ሰማያት ወምድር፤ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ።

ወነአምን፡ ከመ አሓዱ እግዚአብሔር ጸባዖት፡ ረሰየ ዋሕድናሁ ፍጹመ፡ በክዕበተ ህልውናሁ ዘእግዚአብሔር አብእም፣ ዘኮነ፡ በሥርዓተ ሰብሳብ መለኮታዊ።

ወነአምን፡ በትሥልስተ አሓዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር ጸባዖት፣ዘግህደ በተዋሕዶ ህላዌሃ፥ ወበአካላ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንተ ይእቲ፡ መንበረ እግዚአብሔር ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፥ ወኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልድ ዋሕድ፡ እምእግዚአብሔር አብእም፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ መሲሕ፥ ብርሃን፡ ዘእምብርሃን፥ አምላክ፡ ዘእምአምላክ፡ ዘበአማን፤ ዘተወልደ፡ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ እግዚአብሔር አብእም፡ በመለኮቱ።

ዘቦቱ፡ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ፡ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ።

ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ ሰላምነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ፤ ወተሠገወ፤ ወኮነ፡ ብእሴ ፍጹመ፡ በነሢአ ሥጋ፡ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ፡ እምነፍሳ፣ ወመንፈስ፡ እምመንፈሳ፣ እምማርያም፡ እምቅድስት ድንግል፡ ዘተዋሓደት እግዝእተብሔር እም፡ ለመድኃኒትነ፡ በግብረ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ዘበቅድም።

በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፤ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ።

ወሞአ ለዲያብሎስ፡ አቡሆሙ፡ ለሓሰት፡ ዘተሰይመ "ኃጢኣት"፥ ወለእከይ፥ ወለሞት፥ ወለሙስና መቃብር።

ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት።

ዐርገ በስብሓት፡ ውስተ ሰማያት። ወነበረ፡ በየማነ እግዚአብሔር አብእም፥ በመንበሩ ዘበዕሪና።

ዳግመ መጽአ፡ በህላዌሁ ዘመንፈስ ቅዱስ፣ በከመ አሰፈዎሙ ለአርዳኢሁ፣ ወአስተቄጸለ ቀዳሚት ትንሣኤ ሕይወት ዘመንፈስ፡ ለደቂቀ-ኢትዮጵያ፡ ብፁዓን ወብፁዓት፥ ቅዱሳት ወቅዱሳን።

ወይመጽእ በትንሣኤ አካሉ ወበስብሓቲሁ፡ ለኵሉ ፍጥረት ዕልው፡ ዘኵሎን ዓለማት፤ ይኴንን፡ ሕያዋነ፥ ወሙታነ።

ወአልባቲ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡ ዘተሰምየት፡ "ኢትዮጵያ"።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፤ ማኅየዊ ዘበአማን፤ ዘሠረፀ እምእግዚአብሔር አብእም፤ ወዘይነብር በመንበሩ ዘበዕሪና፣ በፀጋመ እግዚአብሔር አብእም፣ ዘንሰግድ ሎቱ፥ ወንሰብሖ፡ ምስለ እግዚአብሔር አብእም፥ ወእግዚአብሔር ወልድ።

ዘነበበ በነቢያት፤ ወዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፤ ወጸጋሁ፡ ዘመልዓ ዓለመ፡ በምሥዋዐ መድኃኒትናሃ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወበቤዛ ሰላመ-መስቀሉ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እምጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብአት ቀደምት፥ ወዘአጽንዓ፡ በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሓዋርያት።

በውስቴታ፡ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤ ወባቲ ይትዌከፉ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡ ኪዳናውያን ወኪዳናውያት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ዘረከብናሃ፡ እምእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት፡ ለስርየተ ኃጢአት።

ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ፡ ዘለዓለም። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

## ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያ።

**ንሕነ፡ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡-**

ነአምን በኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፥ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወሀቦን እግዚአብሔር፡ ለውሉድ ወአዋልድ፡ ዘሰብእ።

አምላክነ፡ ሣረረ ዝንቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፥ ወኢትዮጵያዊት፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ እምሥርዓተ ሰብሳብ፡ ዘአዳም፥ ወሔዋን፡ በዘመነ ፍጥረት ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕያው ሕንጻ ዘሰብአት፡ በቀስተ ደመናሁ፡ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ፡ ዘመልከ-ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት፡ ዘግህደ በፅምረተ አሥራወ ዘርዖሙ፡ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላዊ፣ ከመ ያስተሰነአዎ ኵለንታሁ፡ በኪዳነ ኦሪት።

ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ፥ ወዘተወልደ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት፡ እምዛቲ ሥርው ምልእት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ።

በእንተዝ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት፡ በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፥ ወበሰብእናሃ ለኢትዮጵያዊት፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኀቤሁ፥ ወበኀቤሃ፡ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ።

ነአምን፡ ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ክርስቲያን"፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ "ክርስቶስ"፡ ከመ ውእቱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ካህንነ፥ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፤ ወዘኮነ አርአያሁ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ በልደቱ ዘኮነ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት።

ነአምን፡ ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ፡ "ደቂቀ ኢትዮጵያ"፡ በስመ ዚአሃ፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ"፡ ከመ ይእቲ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዕፀ ሕይወት፥ ወእመ-ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ-ሰማያት ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለእግዚአብሔር ጸባዖት።

ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ፡ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶን፡ ሐመልሚለ፥ ወወርቀ፥ ወቀይሐ፡ ዘተውህበ ለነ እምእግዚአብሔር ፈጣሪነ፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ በዘሕዝብናነ ዘኪዳን ቅዱስ፣ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም።

ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ፡ እምእግዚአብሔር አምላክነ፡ በዘሕዝብናነ ዘኪዳን ቅዱስ፣ ወበዘውእቱ ዘተነግረ፡ በእንተ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፣ በቃለ ትንቢት፡ እንዘ ይብል፡ **"ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"**፣ ወበእንተ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ መፈጽም ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝንቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡ **"ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"**።

ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ፥ ወካህናቲሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ፡ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ፣ ወበእሳት፡ እንበይነ ጸጋሁ፡ ዘኪዳኑ ቅዱስ።

ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ፡ እንበለ ፅርዓት፡ ለስርየተ ኃጢአት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።

ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ ይትአወቅ በምግባሪነ፡ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም፡ በተዋሕዶተ ፍቅርነ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።

ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፤ ወዘመሀረነ፤ ወዘረሰየነ፡ ንዕቀቦ በሀልዎትነ፡ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

## ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡
## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

ኦ አቡነ፥ ወእምነ፥ ወእኅትነ፥ ወእኍነ፥ ወመንፈስነ-ቢጽ እግዚአብሔር! ነአኵተከ እግዚኦ፥ ወንሴብሓከ፤ ንባርከከ እግዚኦ፥ ወንትአምነከ፤ ንገኒ ለከ እግዚኦ፥ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ፤ ንሰግድ ለከ፤ ኦ ዘለከ! ይሰግድ ኵሉ ብርክ፤ ወለከ ይትቀነይ፡ ኵሉ ልሳን።

አንተ ውእቱ፡ አምላከ አማልክት፤ ወእግዚአ አጋእዝት፤ ወንጉሠ ነገሥት። አምላክ አንተ፡ ለኵሉ ዘሥጋ፤ ወለኵላ ዘነፍስ፥ ወለኵሉ ዘመንፈስ።

ወንጼውዐከ፣ በእንተ ዘተወከፍከ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዘ ይብል፡- "አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡-

'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ! ትምጻእ መንግሥትከ! ወይኩን ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፡ ከማሁ በምድር! ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፡ ሀበነ ዮም! ሕድግ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፣ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ! ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት! አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ፡ እምኵሉ እኩይ! እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል፥ ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም።'"

ወበእንተ ዘአብዛኅከ ለነ፡ ኂሩትከ፤ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፤ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፤ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ሥጋነ፥ ወነፍስነ፥ ወመንፈስነ።

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ በምክንያተ ምሥዋዐ መድኃኒትነ፡ ዘእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወቤዛ መስቀለ-ሰላምነ፡ ዘእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።

በእንተዝ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ በምድር፣ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ።
ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ በምድር።
ወመጽአት መንግሥትከ።
ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፡ ከማሁ፡ ኮነ በምድርኒ።

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኵሉ ሀልዎትነ፤ ወአኮ ሲሳይ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ።

ወመጦከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘነሥአ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤ ዘኮነ ለነ፡ ምግበ ነፍስ፥ ወመድኃኒት፤ ዘይረስየነ ሕያዋን ዘለዓለም። ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ወአበሳነ ግሙራ፥ ወዘኢ.ማእዜ። ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ።

ወዐልዓልከነ፡ በልደትነ፡ እምጥምቀት፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት፤ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ።

ወበጸጋከ፡ ዘንሥሓ።

ወአውጻእከነ፡ እመንሱት ዘዘዚአሁ።

ወአድኃንከነ፡ እምኵሉ እኩይ።

ወሞዕክዎ፡ ለዲያብሎስ፡ አቡሃ ለሓሰት።

ወአሰሰልከ፡ ለሞት።

ወበእንተ ዝንቱ፡ አሠለጥከነ፡ ንሄሉ፡ በሕይወተ ቀዳሚት ትንሣኤከ ዘመንፈስ ቅድስት፥ ወበዓለመ ሰንበትከ ዘለዓለማዊት።

ኦ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፥ ወምሕረትከ፥ ወፍቅርከ፥ ወጸጋከ፡ ዘአወፈይከነ፡ በዘኢ.ይትከሃል ይትነገር መጠኖሙ። ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኵሎ ዘንፈቅድ፣ እንዘ አኮ ዘንሰአለከ።

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ ትኄንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘስማ፡ "ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር"፣ ዘትትመራሕ፡

በንግሥትነ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥

ወበንጉሥነ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፥ ዘተብህለ፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፤ ወንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፤ ወንትለአካ፣ ከመ ትትረአይ፥ ወትሰፍን በገሃድ፥ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሜርዎሙ፡ ለእከይ፥ ወለኃጢአት፥ ወለሞት።

እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት። ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

## ጸሎተ ሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም፡
## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

አ እግዝእተብሔር ማርያም እምነ፥ ወመድኃኒትነ!

ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ።

ድንግል በመንፈስኪ፣ ወበነፍስኪ፣ ወበሥጋኪ። ይደልወኪ ዝ ሱላሜ፣ እስመ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ።

አንቲ ይእቲ፡ ሔዋን ቅድስት፤ ወቡርክት፡ እምኵሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ፡ ዘዕፀ ሕይወት፣ በዘውእቱ ኮነ፡ አዳምሁ ቅዱሰ።

ተፈሥሒ! አ ንግሥትነ፡ በሰማይ፥ ወበምድር!

እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፡ እንዘ ይብሉኪ፡ "**ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!**"፥

ወንሕነኒ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "**እምነ ጽዮን!**"

ንሴብሓኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ አ ምልዕተ ጸጋ!"

እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ መድኃኒትነ።

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ክመ እምኄነ፡ ማሕፀንተኪ፡

በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤

እስመ አንቲ ይእቲ፡ እምነ ዘምሕፅና፤

ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡

በቃለ አማሕፅኖ ዘወልድኪ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ አምላክነ፥ ወሰላምነ።

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘተገብረት ለነ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

# ቃለ አሚኖት፡ ዘደቂቀ ኢትዮጵያ



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ።

---

አነ______________________________፥ ወስምየ ዘክርስትና__________________________________________፥
ወልደትየ ዘኮነ በወርኃ_________________፥ በ________ዕለት፥___________________________________ዓ. ም.
በሀገረ ______________________፤ዮም፡ በዝ ወርኃ____________፥ በ________ዕለት፥__________ዓ. ም.

እቀውም፡ በቅድመ መናብርት ዘእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወዘእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በአምልኮተ ጽድቅ ዘመንፈስ ቅዱስ፤ ወናሁ አሰምዕ ስምዕየ በአጽንዖት፣ እንዘ እብል፡-

“አነ ውእቱ ኢትዮጵያዊ/ት ዘኪዳን ቅዱስ፡ ዘእሄሉ፡ በዐቂበ ርትዕት ሃይማኖትየ፡ ጽሪት፡ በምስጢረ ተዋሕዶ፡ እንተ ተመሥረት፡ በዝንቱ ኪዳን ቅዱስ፡ ዘውእቱ መዝገቦሙ ለሰብዓቱ ኪዳናት፡ ዘተካየዶን እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ፣ እላንቱ፡ ዘተወጥና፡ በአዳም ወሔዋን፥ ወተሓደሳ በሰብእናሆሙ ለኖኅ፥ ወለመልከ ጼዴቅ፥ ወለአብርሃም፥ ወለሙሴ፥ ወለዳዊት፡ እስከልደተ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዘተፈጸማ በዛቲ ትስብእት፥ ወዘተግህደት በምግባርየ፥ ወዓዲ ዘእሄሉ በአንጽሖተ ርእስየ፡ በንስሓ፥ ወበአጽድቆተ ሰብእናየ፡ በተመጥዎተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ።

“ኦ አምላኪየ፥ ወመድኃኒትየ፥ ሃይማኖትየ ወሀገርየ፥ እምየ ወንግሥትየ፡ እግዝእተብሔር እም፡ድንግል ማርያም! እሰግድ ቅድመ መንበርኪ፤ ወአቀርብ ለኪ አምኃየ ዘስባሔ፡ በቃለ ገብርኤል መልአክ ቅዱስ፡ እስመ በፍቅርኪ ወበረድኤትኪ፡ ኮንክኒ ማሕፀንትየ፡ ከመ እጽናዕ በኢትዮጵያውናየ ዘቅዱስ ኪዳን፡ በኵሉ መዋዕልየ።”

“ኦ ፈጣርየ ወሰላምየ፥ ካህንየ ወንጉሥየ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ! እሰግድ ቅድመ መንበርከ፤ ወእሴብሓከ፤ እስመ አብቍዐተኒ ከመ በክሡት አሰምዕ፡ ዝ ስምዕ፡ በተአምኖትየ ዘቃልከ መለኮታዊት፡ ዘትብል፡ **‘ኵሉ ዘየአምን ብየ፡ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ አአምኖ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት፤ ወዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ እክሕዶ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት።’ አሜን።”** (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

## የኢትዮጵያ፡ የሃይማኖት ጸሎት።

እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡-

አንድ አምላክ በሚኾን፡ በአሸናፊው እግዚአብሔር እናምናለን። እርሱም፡ ኹሉን የያዘው፤ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውንም የፈጠረው ነው።

አንድ አምላክ የኾነው፡ አሸናፊው እግዚአብሔር፡ ይህን አንድነቱን፡ እርሱ በሠራው፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር አብእም ኹለትነት፡ ፍጹም እንዳደረገው እናምናለን።

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት፡ የአሸናፊው እግዚአብሔር ቅድስት ሥላሴ ዙፋንና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የተዋሕዶ አኗኗርና አካል እንደተገለጠ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የእግዚአብሔር አብእም ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን።

እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ፡ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከእግዚአብሔር አብእም ጋራ የሚተካከል፥ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

በእርሱም፡ ኹሉ ኾነ። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም።

ስለእኛ ስለሰዎች፥ ስለሰላማችን፡ ከሰማይ ወረደ። እግዚአብሔር እም፡ ስለመዳናችን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር ከተዋሓደቻት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን፤ ከመንፈሷም፡ መንፈስን ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ።

በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ።

"ኃጢአት" የተባለው፡ የሓሰት፤ የክፋትና የሞት፤ የመቃብር-መበስበስም አባት የኾነውን ዲያብሎስን፡ ድል አደረገው።

በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ።

በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ።

በእግዚአብሔር አባቱና እናቱም ቀኝ፡ በእኩያ ዙፋኑ ተቀመጠ።

ለደቀ-መዛሙርቱ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሉን በመፈጸም፤ በመንፈስ ቅዱስ ህልውናው ተመልሶ መጣ። የመጀመሪያዋን መንፈሳዊት የትንሣኤ ሕይወትም፡ ለብፁዓንና ለብፁዓት፤ ለቅዱሳትና ለቅዱሳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ አቀዳጀ።

በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድም፡ በትንሣኤ አካሉና በክብሩ ምስጋና፡ ለመላው ከሃዲ፡ የዓለማቱ ኹሉ ፍጥረት፡ ዳግመኛ ይመለሳል።

"ኢትዮጵያ" ለተባለችው መንግሥቱም፡ ፍጻሜ የላትም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን።

እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጠው እና ከእግዚአብሔር አብእም የሠረፀው፤ በእግዚአብሔር አብእም በስተግራ ባለው፡ የእኩያ ዙፋኑ የተቀመጠው፣ ከእግዚአብሔር አብእም እና ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ የምንሰግድለት፣ የምናመሰግነውም፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው።

በነቢያት ዐድሮ የተናገረው እና በሓዋርያት ላይ የወረደው፣ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የማዳኗ ምሥዋዕነት እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመሰቀሉ ሰላም ቤዛነት፡ ዓለሙን፡ በጸጋው የሞላው፡ እርሱ ነው።

እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን።

እርሷም፡ በነቢያት ቃል ያጸናት እና በሓዋርያት ጉባኤ የፈጸማት፥ ካህናት፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውን፡ የእርሱን፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት የሚያቀርቡባት፥ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆችም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች የሚቀበሉባት ናት።

ኃጢአት በሚሰረይባት፥ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት በተቀበልናት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## የኢትዮጵያ፡ የቃል ኪዳን ጸሎት።

**እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡-**

እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፣ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፣ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን የኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያዊት ሕያው ሰውነት፡ በመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤

ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቍርባን እና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤

**በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤

**በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የተወለደው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእርሷ በነሣው ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።

ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው እና ኢትዮጵያዊቷ ሰውነት ገዝፋ፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷን እና ቤተ ምልክናዋን፡ በምስጢረ-ተዋሕዶ፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን፡ "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በቀደመው ዘመን፡ ለእርሱ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካም እና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ያሰኘችን፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ አሸናፊውን እግዚአብሔርን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕይወት ዛፍ፥ የሕያዋን እናትና፥ ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

በሦስቱ ታላላቅ ኅብረ-ቀለማት፡ በአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ያሸበረቀው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታችን፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከፈጣሪያችን እግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የተነገረው፡ **"ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!"** የሚለው ትንቢታዊ ቃል እና የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተነገረው፡ **"የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!"** የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታችን፡ ከአምላካችን እግዚአብሔር ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች [ነጋሾች] እና ካህኖች [አገልጋዮች] እንደኾንን እናምናለን።

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን፡ ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፣ ኃጢአታችንን፡ ዘወትር በንስሓ እያጠራን፣ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውንም ሥጋና ደም እየተቀበልን፡ መኖር እንዳለብን እናምናለን።

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ባለን የተዋሓደ ፍቅር ኾነን፡ በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን የጻፈው፤ ያስተማረንም፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት።

አባታችንና እናታችን፥ እኅታችንና ወንድማችን፥ ባልንጀራ መንፈሳችንም፡ እግዚአብሔር ሆይ!

አቤቱ እንቀድስሃለን እናመሰግንሃለንም፤ አቤቱ እናወድስሃለን፤ እንታመንብሃለን፤ አቤቱ እናገንሃለንም፤ ለቅዱስ ስምህ እንታዘዛለን፤ እንሰግድልሃለን፤ ጕልበት ኹሉ፡ ለአንተ ይሰግዳል፤ አንደበትም ኹሉ፡ ወደአንተ ይጮሃል።

አንተ፡ የአማልክት አምላክ ነህ፤ የገዢዎች ገዢ ነህ፤ የንጉሦችም ንጉሥ ነህ። አንተ፡ የሥጋዊው ኹሉ፥ የነፍሳዊው ኹሉ፥ የመንፈሳዊውም ኹሉ ወገን ፈጣሪ ነህ።

ልጅህ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ "እናንተ ስትጸልዩ፡ 'የሰማዩ አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ! መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ በሰማይ እንደኾነ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ይኹን! የየዕለቱን ምግባችንን፡ ስጠን ለዛሬ! ኃጢኣታችንንና በደላችንን፡ ይቅር በለን! እኛም የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል! አቤቱ ወደፈተና አታግባን! ከክፉው ኹሉ፡ አድነን እንጂ! መንግሥት፡ የአንተ ናትና፥ ኃይልና ምስጋናም፤ ለዘለዓለሙ።' በሉ!" ብሎ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡

በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ፡ አኹን፡ እኛም፡ ስምህን እየጠራን፡ እናመሰግንሃለን።

በመዳናችን ምሥዋዕ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በሰላማችን የመስቀል ቤዛ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን።

ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም፡ የምትኖር ኾንህ።
ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ።
መንግሥትህም መጣችልን።
በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ፡ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህ።

ለዘለዓለም ሕያዋን የሚያደርገን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንንም፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን።

እርሱም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣው ነው።

በእርሱም፡ ኃጢኣታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደመሰስህ። ፈጽመህም ይቅር አልኸን።

እኛም፡ የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለመኾን በበቃንበት፣ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት፡ ባቀዳጀኸን፡ የጥምቀት ልደታችን አከበርኸን።

የንስሓንም ጸጋ አደልኸን።

ከማናቸውም ፈተና አወጣኸን።

ከክፉው ኹሉ አዳንኸን።

የሓሰቱን አባት ዲያብሎስንም፡ ድል አደረግህ።

ሞትንም አስወገድህ።

ልዩ በኾነችው፡ በመጀመሪያዋ የመንፈስ ትንሣኤ ሕይወት እና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም ለመኖር አበቃኸን።

እግዚአብሔር ሆይ! መጠኑ፡ ሊነገር ስለማይቻለው ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም፡ የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

**"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"**፡ ክፋትን፥ ኃጢኣትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን።

እርሷም፡ **"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ታደርሳለች!"** በተባለችው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ንግሥትነት እና **"የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!"** በተባለው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ንጉሥነት የምትመራው፥ እኛም፡ ዛሬ የምንኖርባት፣ የምናገለግላትም፡ የእውነት መንግሥትህ ናት።

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ የአንተ ናቸው፤ ዛሬም፣ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት።

እናታችንና መድኃኒታችን እግዝእተብሔር ማርያም ሆይ!

በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን።

በመንፈስሽ እና በነፍስሽ፣ በሥጋሽም፡ ድንግል ነሽ። በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ነሽና፡ ይህ ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል።

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፣

አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ።

ቀድሞ በነቢያት፡ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!" የተባልሽ፥

እኛም፡ "እናታችን ጽዮን!" ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ!

እግዚአብሔር፡ አንቺን፡ የመዳናችን ምክንያት አድርጎ፡

ኪዳነ ምሕረቱን፡ ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡

"ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ብፅዕት ነሽ!" እያልን፡ ዘወትር እናመሰግንሻለን።

በአምላካችንና በሰላማችን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡

አንቺ፡ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥

እኛም፡ ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡

ከተወደደው ልጅሽ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ያልተለየው እናትነትሽ፡

ከእኛም፡ ምንጊዜም፡ እንደማይለየን እናምናለን።

በዚህ ኹሉ፡ ለተደረገልን ቸርነት፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

# የኢትዮጵያ ልጆች፡ የታማኝነት ማረጋገጫ ቃል



የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ፤
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፤
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዝእተብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

እኔ፡ ________________________፥ በክርስትና ስሜ ___________________________የተባልሁ፥ በ________________ቀን፥_____________ዓ. ም. በ________________________________የተወለድሁ፡ ዛሬ፡ በዚህ በ_______________ቀን፥___________ ዓ. ም. በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ መንበሮች ፊት፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ቆሜ፡ እንዲህ እያልሁ፡ የምስክርነት ቃሌን በማረጋገጥ እሰጣለሁ።

"እኔ፡ በኢትዮጵያ የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች ውስጥ እንደተገለጸው፡ በአዳምና ሔዋን ተጀምሮ፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት በኩል እየታደሱ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ድንግል ማርያም እስከተወለደው፡ እስከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ደርሶ በተፈጸመው፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉትን፡ ሰባቱን ኪዳናት በአጠቃለለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተመሥርታ የቆመችውን፥ በምስጢረ ተዋሕዶ የጠራችውንና የቀናችውን ሃይማኖቴን ጠብቄና በምግባር አጽንቼ፡ ራሴን፡ በንስሓና በሥጋ ወደሙ እያጸደቅሁ የምኖር፡ **የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ/ት ነኝ።**

"አምላኬና መድኃኒቴ፥ ሃይማኖቴና አገሬ፥ እናቴና ንግሥቴ፡ እግዝእተብሔር እም፡ድንግል ማርያም ሆይ! በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ጸንቼ እኖር ዘንድ፡ በፍቅርሽና በረድኤትሽ ስላልተለየሽኝ፡ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ በመንበርሽ ፊት ሰግጄ፡ የምስጋና ሰላምታዬን አቀርብልሻለሁ።

"ፈጣሪዬና ሰላሜ፥ ካህኔና ንጉሤ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ!"**በሰው ፊት፡ በእኔ አምኖ ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ።"** ያልከውን መለኮታዊ ቃልህን አምኜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን የምስክርነት ቃል፡ በይፋ እንድሰጥ ስላበቃኸኝ፡ በመንበርህ ፊት እየሰገድሁ አመሰግንሃለሁ። አሜን።" (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

# THE ETHIOPIAN CREED

We, Children of Ethiopia, believe in One God Igziabher, Almighty, Who Possesses All, Maker of the Heavens and Earth, the Visible and the Invisible.

We belive that The One God Igziabher Almighty made His One-ness to become manifest in The Unity and Duality of God The Father-Mother, in Accordance with the Divine Sacrament of Matrimony.

We believe in The Trinity of The One God Igziabher, embodied in The Co-existent and Incarnate Goddess The Mother Virgin Mary, Who is The Throne of The Holy Trinity –God The Almighty, and Ethiopia: The Kingdom of God Igziabher.

We believe in God The Son, Jesus Christ, One Lord, The Only Begotten Son of God The Father-Mother, Who was with Him before the creation of the world. He is Light from Light, True God Igziabher from True God Igziabher, Begotten, NOT made, and, in His Divine Essence, EQUAL with His God Father-Mother. All things were Made by Him, and Without Him, Nothing Whatsoever was Made, in Heavens or on Earth.

He Came Down from Heavens for Our Sake, for the Sake of Humanity, and for the Sake of OUR PEACE. He was Incarnate in the Womb of The Holy Virgin Mary with Whom Goddess The Mother is UNITED, for OUR SALVATION, by the preceding Divine Work of God The Holy Spirit, and, God The Son, acquiring the Human Soul, Flesh and Spirit from Her, became the Perfect Man, Jesus Christ.

In the Days of Pontius Pilate, He Suffered, was Crucified, Died and was Buried for Our Sake. He triumphed over Satan who is the father of lie, which is designated as sin, and of evil, and of death, and of the corruption in the tomb. And He Rose from the Dead on the Third Day, Ascended in Glory into Heavens and Sat on His Throne of Equal Status at the Right-Hand Side of His God Father-Mother.

Fulfilling His Promise to His Disciples, He Came back in His Nature of The Holy Spirit to Bestow upon The Blessed and Consecrated Children of Ethiopia, the First Spiritual Resurrection. And For the Rest of His Creation of all the Worlds that denied Him, He will Come Again in His Resurrected Body and in His Glory to Judge the Living and the Dead. There is NO END to His Kingdom, ever identified as "Ethiopia".

We believe in God The Holy Spirit. He is the True and the Life-Giving Spirit Who Proceeds from God The Father-Mother, and Whom, we Worship and Glorify with God The Father-Mother and God The Son. Seated on His Throne of Equal Status at the Left-Hand Side of God The Father-Mother, He Spoke through the Prophets, Descended upon the Apostles and, by the Redeeming Altarage of The Goddess Mother Virgin Mary and the pacifying Atonement of The Crucified God The Son Jesus Christ, Filled the World with His Grace.

We believe in the One Holy Ethiopia: The Kingdom of God Igziabher that was founded by the Divine Incarnate Word, God The Son Jesus Christ, initially in the Hearts of the Patriarchs and Matriarchs, and later sustained by His Divine Messages through the Prophets, and finally brought to perfection through the Holy Spirit by His convocation of the Apostles;

And where priests offer His Holy Flesh and Sacred Blood That He incarnated from The Goddess Mother Virgin Mary as Sacrifice for Our Communion with God Igziabher, and where the Sacramental Blessings of the Holy Spirit are bestowed upon and communicated to all Covenantal Children of Ethiopia.

We believe in One Baptism that We received from The Son God Jesus Christ by The Holy Spirit and Fire for the Remission of sins.

We believe in the Resurrection of the dead and the Life in Eternity, world without end. Amen.

# THE TESTIMONIAL OF THE ETHIOPIANS ON THE HOLY COVENANT

We, Children of Ethiopia, believe in our Ethiopianhood of the Holy Covenant that embodied and conserved the Seven Divine Covenants GOD Igziabher granted to humanity, men and women.

Our God Igziabher, in the Era of the Genesis, founded the Ethiopian Living Human Entity, primarily, on the Covenant of the Soul of the Male and the Female, through the Matrimony of Adam and Eve. Then, He raised it, through Noah's Rainbow, Melchizedek's Offering and Abraham's Circumcision, to the next stage of its eschatological growth.

In the transitional Era of the Old Testament, He developed it, through Mose's Ark and David's Throne, to the finishing level that caused to bring about, under the Covenant of the Law, the genealogical union of the Ethiopian Queen Makkedda and the Israelite King Solomon.

Finally, in the Era of the Everlasting Life, He brought it to completion with the Sacrificial Body and Blood of His God Son Jesus Christ, born of and incarnated from The Goddess Mother Virgin Mary, who is the pure seed descended from that preordained genealogical union, thus culminating in the Ethiopian Person with the Eternal Crown of the Covenant of the Holy Spirit.

We believe that Ethiopia, as such, represents the Kingdom of God Igziabher, embodied in the unity of the person of the Male and Female Ethiopians of the Holy Covenant, each constituting the three Houses of the People, of the Government and of the Priesthood achieved through Her Precepts of TEWAHDO [Unity in Duality and Trinity].

We believe that God The Son Jesus Christ, in Whose Name, meaning "Christ", we are called "Christians", is our Eternal Priest and King, in the Order of Melkizedek, the Ethiopian, who, born of the triple Seed that sprung from Shem, Ham and Japhet, appeared in the beginning of time as The Precursor and Image of God The Son Jesus Christ.

We believe that The Goddess Mother Virgin Mary, Who is the Personification of Ethiopia, and in Whose Name we are called "Children of Ethiopia", and as One Who Bore God The Almighty, is the Tree of Life, the True Mother of the Living, the Eternal Ark of the Covenant, and our Queen in Heavens and on Earth.

We believe that the Tri-Coloured brilliant Banner of Green, Yellow and Red, symbolizing those dominant colours of the Sign of the Rainbow, is our Eternal National Flag entrusted to us, as People of The Holy Covenant, by Our Creator God Igziabher through The Covenant of Noah.

We believe that the Prophetic Word that reads: **"Ethiopia Reaches out Her Hands to God Igziabher!"** and attributed to The Goddess Mother Virgin Mary, and the Divine Word that says: **"The Triumphant Lion of the Tribe of Judah!"** and ascribed to God The Son Jesus Christ Who is the Ultimate Manifestation of the Holy Covenant, and that both Words of the Holy Spirit are Our Eternal Divine Seal we received from Our God Igziabher, as a Nation of The Holy Covenant.

We believe that the Crowning and Exaltation of our Spiritual Birth from God Igziabher, through the Grace of The Holy Covenant in the Holy Spirit and Fire, entitled us to be Heirs (kings and queens) and Servants (priests and priestesses) of the Kingdom of God Igziabher.

We believe that, in order for us to maintain such Divine birthright privilege, to confirm our inheritance of God Igziabher's Kingdom and to continue rendering our pertinent services, it is our constant commitment to Absolve our Sins through Incessant Repentance and Partake the Holy Communion of Our God The Son Jesus Christ that He incarnated from The Goddess Mother Virgin Mary.

We believe that the Genuine Manifestation and the Distinctive Identification of our Faith in the Ethiopianhood of The Holy Covenant are best demonstrated by the typical Ethiopian Deed in the Ethiopianhood of The Holy Covenant that we simultaneously perform in consideration and reflection of our unified LOVE for both The Goddess Mother Virgin Mary and God The Son Jesus Christ.

We believe that it is our God Igziabher Who, in accordance with His Word of The Covenant, **inscribed in our hearts, taught us and made us to preserve in our lives** this Ethiopianhood, Which is the Embodiment of the Holy Covenant. Amen.

## PRAYER OF THE ETHIOPIANS IN GLORIFICATION OF THE LORD

Our Father, Mother, Sister, Brother and Companion Spirit, God Igziabher! We thank You, and praise You O The Divine! We glorify You and trust You, The Almighty! We worship You. All powers bow, and all tongues raise their voices unto You. You are The Only God Igziabher of gods, Supreme Sovereign of sovereigns, and Eternal King of kings. You are the Creator of all physical, intellectual [of the soul] and spiritual beings. Now, we invoke Your Name in the same way Your Son God Jesus Christ taught us to say, **"Our Father who art in Heaven, Hallowed be Your Name. Your Kingdom come. Your Will be done on Earth as it is in Heaven. Give us this day our daily bread. And forgive us our debts, as we forgive our debtors. And do not lead us into temptation; but deliver us from the evil one. For, Yours is The Kingdom, and The Power, and The Glory, forever. Amen."** and, through Whose atonement You gave us the ANSWER to our supplication in that prayer.

Yes, You provided us with everything that pertains to our material, mental and spiritual needs for the body and the soul as well as for the spirit. Your generosity for us is bountiful; Your mercy, complete; Your love, perfect, and Your grace, overflowing.

Through the Redeeming Altarage of Our Goddess The Mother Virgin Mary and the Atonement for Peace of The Crucified God The Son Jesus Christ, the Grace of the Holy Spirit Descended over and Filled the Whole World. Thus, today You reside not only in Heavens, but on Earth as well. Your Name is Hallowed also on Earth. Your Will that is Done in Heavens is Done also on Earth. Your Kingdom has Come and is Revealed on Earth.

By Your endowment of Nature, we recognized that You have arranged, not only for our Daily Bread, but also for the entire life-long provisions of our Bodily Needs.

You gave us, on daily basis, the Holy Sacrament of the Flesh and Blood of Your God Son Jesus Christ that He incarnated from The Goddess Mother Virgin Mary as nourishment for our Soul, and as an assurance for our salvation and eternal life. Through the same Sacrament, You exonerated us completely from our sins and iniquities once for all, and empowered us to forgive the debts of our debtors.

For us to be Your Children, You granted us the Exaltation of the Birth of Baptism in The Holy Spirit and Fire, and the Sacrament of the Grace of Penance. You Spared us from Every Temptation, Delivered us from Evil, and Overthrew the Powers of the Devil, the Father of Lie, and eliminated Death that Dominated our Lives. Finally, You Ordained for us the Honour and the Privilege to Live in the Rapture of Your Holy Resurrection and in the World of Your Eternal Sabath.

O The Almighty God Igziabher! We are Always Grateful to You for Your Inexpressible Generosity, Mercy, Love and Grace, as well as for all our Needs that You Provided us Before we Even Ask You.

We remain Waiting for the Time You Promised us to Come, When Your Kingdom of Truth, designated as "Ethiopia: The Kingdom of God [Igziabher]"in which we are Now Blessed to Live and Serve under Our Reigning Queen Goddess The Mother Virgin Mary, personified in the Prophetic Word as **"Ethiopia Reaches out Her Hands to God Igziabher!",** and the Kingship of God The Son Jesus Christ, epitomized as **"The Triumphant Lion of the Tribe of Judah",** will Prevail and Destroy Evil, Sin and Death Completely; and When It Actually Reveals Itself to the Material World and Universally Rules over the Whole Realms of Creation.

Power, Glory and Kingdom are Yours, Today as Ever and Forever, World Without End. Amen.

# PRAYER OF THE ETHIOPIANS

# IN EXALTATION OF THE HOLY MOTHER.

Our Goddess Mary The Mother and Saviour! With the Words of Greeting of the Angel Saint Gabriel, we Bow to You in Solemn Worship saying, "Hail, O Favoured One!" You are Virgin in Spirit, in Soul and in Body. Because of Your Perfect Chastity, You Became the Mother of the Almighty God Igziabher. And so, You Deserve such Blissful Salutation.

Your Womb Bore the Holy Adam Who is the Sacred Fruit of the Tree of Life. Hence, You are the Holy Eve, the Chosen and the Blessed One among all the women.

In the early times, the Prophets spoke of You as **"Ethiopia Reaches out Her Hands to God Igziabher!"**, and we addressed you as **'Our Mother Zion'**.

Rejoice, O Our Queen of Heavens and Earth! God Igziabher, through Your Instrumentality Fulfilled His Promise of our Salvation and Granted His Eternal Covenant of Mercy to His Creation. And so, we Always Praise You saying. "You are The Blessed, Full of Grace."

In the Words of Your God Son, and our God and Peace Jesus Christ, we are Your Sons and Daughters, Commended to Your Maternal Care; and You are our Holy Mother, Entrusted to our Spiritual Dedication. Thus, we believe Your Motherhood that has Never Forsaken Your Beloved God The Son Jesus Christ, So will It Always Be with us.

We thank Our Gracious God Igziabher, the Most High, for His Benevolence of Such Magnitude. World without end, Amen.

\+ + +

# <u>Declaration of Allegiance of the Ethiopian</u>



The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
The Son God Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melke-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

Ethiopia Reaches Out Her Hands to God Igziabher
Goddess The Mother Virgin Mary
Mother of Our Messiah and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

I____________________________with my Christian Baptismal Name of __________________, born in________________________on__________________, standing in front of the altars of Goddess The Mother Virgin Mary and of God The Son Jesus Christ, on this day of _______________, __________, in the Worship of Truth and The Holy Spirit, do hereby Solemnly Attest and Declare:

That I read and knew, learned and understood, believed and accepted, along with the Prayers of Glorification to the Lord and of Exaltation to the Virgin Mary, the Creed and the Testimonial to the Holy Covenant that was initiated by Adam and Eve, and transmitted through the faithful and dedicated Persons of Noah, MelkiZedeq, Abraham, Moses and David, to the End of Time at which juncture It culminated in and revealed by the Incarnation of The Son God Jesus Christ in the Womb of The Goddess Mother Virgin Mary as the Perfect and Complete Embodiment of the Seven Covenants, all, as specified and enshrined in the Four Sacred Scripts of Ethiopia: The Kingdom of God Igziabher, attached herewith.

That, as an Ethiopian of The Holy Covenant who kept his/her Tewahdo faith and partakes the Holy Communion in constant penitence, I will abide by and live upto the precepts of the Same in the fullness of my whole physical, moral and spiritual being and existence, in this world and in the world to come.

O, Mother Goddess, my Saviour, my Faith and Country, Mother and Queen Holy Virgin Mary, Kneeling in Worship before Your Eternal Throne, I humbly offer You my Greetings of Praise in the Words of Saint Gabriel the ArchAngel, trusting in Your Loving Care and Protection that would sustain me in my plight to remain steadfast in preserving my Ethiopian identity of the Holy Covenant.

O, My God, My Peace and Priestly King Jesus Christ! I thank You, prostrating in supplication before Your Eternal Throne, for empowering me to give openly such witness of my faith of Ethiopianness of the Holy Covenant, in trust and in accordance with your Divine Word that says, **"Whosoever therefore shall confess me before men, him will I confess also before my Father which is in Heaven. But whosoever shall deny me before men, him will I also deny before my Father which is in Heaven."** Amen! (Matt. 10/32-33)

ተዐውደ፡ በነሓሴ ፲፯ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ \+ \+